# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ



5ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አምስተኛ ክፍል


**አዘጋጅ ፡-**

- ተዋበ ታደሰ
- ሲሳይ ከበደ
- ታደሰ ይስማው
- ታምራት አብራሀም

**አርታኢ፡-**

- ምህረቱ ዋሴ

**ሰዓሊ፡-**

- ሲሳይ ከበደ

**ኖታ ቀራጭ፡-**

- ተዋበ ታደሰ

**የጥራት ተቆጣጣሪ (ፓናሊስት) ፡-**

- ተክለማሪያም ጥላሁን
- ተዋበ ታደሰ

**አጽዳቂ (ቫሊዴተር) ፡-**

- ሜላት መካሻ
- ለምለም ደግፌ
- ፍቅሩ አርፋሶ
- አሰጋኸኝ ጉዬ
- ሰውነት ቶማስ

**ዲዛይንና ሌይአውት፡-**

- ሲሳይ ታገሠ



2014 ዓ.ም

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ

# © ቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው።

2014 ዓ.ም

ሀዋሳ

# ማውጫ


## ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

### 1. የእይታ እና የትወና ጥበባት አላባውያን ........................................ 1

1.1. መግቢያ........................................1
1.2. የሙዚቃ አላባውያን........................................17
1.3. መሰረታዊ የመድረክ ተውኔት ጥበብ (ቴአትር) አላባውያን........................................24
1.4. ቀላል የተንቀሳቃሽ ምስል መቅረጫ ዘዴዎች ........................................27
ማጠቃለያ........................................28
የማጠቃለያ መልመጃ........................................29

## ምዕራፍ ሁለት ........................................30

### 2. ፈጠራዊ አገላለጽ ........................................30

2.1. የሙዚቃ ኖታዎችን መሰየም ብሎም መጻፍ ........................................31
2.2. የባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ እና ከተዘጋጁ ማተሚያዎች ህትመት መስራት ............38
2.3. ቴአትርን በመድረክ አልባሳት እና ቁሳቁስ መስራት........................................43
ማጠቃለያ........................................48
የማጠቃለያ መልመጃ........................................48

## ምዕራፍ ሦስት........................................50

### 3. የእይታ እና የትወና ጥበብ ጭብጦች........................................50

3.1. ሃገረሰባዊ ዜማዎችና የውዝዋዜ (የዳንኪራ) አይነቶች........................................51
3.2. የዕይታ ጥበብ አይነቶች በታሪክ ውስጥ (የዋሻ እና የቀለም ቅብ) ጥበብን መለየት......55
3.3. ሃገረሰባዊ ታሪኮችን መንገር........................................58
ማጠቃለያ........................................63
የማጠቃለያ መልመጃ........................................64

## ምዕራፍ አራት........................................65

### 4. ማስተዋወቅ........................................65

4.1.... በትውን ጥበብ ውስጥ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን መወያየት ..................66
4.2.... የእይታ ጥበብ እና ዕደ-ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው አስፈላጊነት......................68
ማጠቃለያ........................................72
የማጠቃለያ መልመጃ........................................73

## ምዕራፍ አምስት ........................................74

### 5. መስተጋብር ........................................74

5.1.... ሰርቶ ማሳየት ........................................75
5.2.... በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ምልክቶች እና ዓርማዎች........................................80
ማጠቃለያ........................................83
የመልመጃ ጥያቄዎች........................................83
ዋቢ መጽሐፍት ........................................84

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የእይታ እና የትወና ጥበባት አላባውያን

### 1.1. መግቢያ

የአምስተኛ ክፍል የእይታ ጥበብ አላባውያን አዲስ ከተዘጋጀው ስርአተ-ትምህርት እና ፍኖተ-ካርታ አኳያ የተማሪዎችን እድሜና የትምህርት ደረጃ በማገናዘብ እውቀት እና ክህሎት ለተማሪዎች በመስጠት ዘርፈ-ብዙ ጥበባዊ እውቀትን እንደሚያስጨብጥ ይታመናል፡

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥም የእይታ ጥበብ አላባውያን አንድን ስነ-ሥዕል ለመሳል (ለመስራት) የሚያስፈልጉንን እና የሚጠቀሙንን ነገሮች በአግባቡ ተጠቅመን እንድንሰራ የሚረዳን ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ የእይታ ጥበብ አላባውያን በስነ-ጥበብ ስራ ላይ መሰረታዊ የሆኑ አጋዥ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚሳሉና የሚቀረጹ ሆነው ለተማሪዎች በተሻለና ግልጽ በሆነ መንገድ የቀረቡ ናቸው፡፡ የእይታ ጥበብ አላባውያን ተብለው በዚሁ ክፍለ-ትምህርት የተካተቱት መስመር፣ ዝርግ ቅርጽ፣ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ጥቁረት/ንጣት፣ ለስላሳ/ሸካራ እንደዚሁም መጠን እና ድግግሞሽ ናቸው፡፡

ሌላው በዚሁ የትምህርት ክፍል የተካተተው እና የትውን ጥበብ አካል የሆነው ሙዚቃ ነው፡፡ ሙዚቃን ተወዳጅና ተፈላጊ ካደረጉት ነገሮች አንዱ ምት (ሪትም) ነው፡፡ ለሙዚቃ ቀርቶ ለአነጋገር ስልት እንኳን ንግግሮችን ለዛና ውበት የሚሰጥ በመሆኑ ምት (ሪትም) ተፈላጊነቱ ታላቅ ነው፡፡ የጊዜ ቆይታንና የሙዚቃ ድምጽን የሚያመለክቱ ኖታዎች ከነ እረፍት ምልክቶቻቸው በውስጡ አሉ፡፡ ኖታዎች ከነ እረፍት ምልክቶቻቸው ድምጽ የሚቆይበትን ጊዜ ሊለኩ ይችላሉ፡፡ የቀን ውሎ የሚለካው በሰዓት እንደመሆኑ መጠን ድምጽም ቆይታው የሚለካው በምት (ሪትም) ነው፡፡ ምት ደግሞ በኖታዎች እና በእረፍት ምልክቶቻቸው ይገለጻል፡፡ የቀላል ምቶችን ጽንሰ-ሀሳብ በመረዳት በጭብጨባና በእግር ምት ቀላል ልምምዶችን በመስራት ቀስ በቀስ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለመጫወት ያስችላል፡፡

ተማሪዎች የሙዚቃ ኖታዎችን ከነ እረፍት ምልክቶቻቸው የመጫወትን ችሎታን ታዳብራላችሁ:: በተጨማሪም የድምጽ ከፍታ/ዝቅታ (ዳይናሚክስ)፣የድምጽ መወፈር/መቅጠን/መካከለኛ መሆን (ፒች)፣የድምጽ ፍጥነትና እርጋታ (ቴምፖ) የመሳሰሉት ጽንሰ-ሃሳቦች በዚሁ የትምህርት ምእራፍ ውስጥ የተካተቱ ስለሆነ ትኩረት ሰጥታችሁ በመከታተል የሚጠበቅባችሁን የተማሪነት ሚና እንድትጫወቱ ይጠበቃል:: በተጨማሪም ውዝዋዜ ሌላው ከሙዚቃ ስሜት ጋር ተያይዞ ተማሪዎች በአግባቡ ሊረዱት የሚገባ ጽንሰ-ሃሳብ ሲሆን በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥም ተማሪዎች ስለ ውዝዋዜ እንዲረዱ ሊያደርጉ የሚችሉ መሰረታዊ ሃሳቦች ተካተዋል::

በዚህ ክፍለ-ትምህርት ላይ ተካቶ የሚገኘው እና የትውን ጥበብ አካል የሆነው የመድረክ ተውኔት ጥበብ (ቴአትር) ሲሆን በውስጡም የተለያዩ አላባውያንን ያካተተ ነው:: ይህንንም ጽንሰ-ሃሳብ ተማሪዎች ተረድተው የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይጠበቃል: : በመድረክ ተውኔት ጥበብ (ቴአትር) ውስጥ የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ፣የተውኔት ዘውጎች፣የተውኔት ድርሰት አላባውያን፣ታሪክ፣ገጸ-ባህሪ እና ትወና የመሳሰሉት በዚህ የትምህት ክፍል ውስጥ የተካተቱ ጭብጦች ናቸው::

በዚህ የትምህርት ክፍል መጨረሻ ተማሪዎች ቀለል ያሉ የትውንና የእይታ ጥበብ አላባውያንን ይለያሉ  የእይታ ጥበብ አላባውያን

## መግቢያ

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥም የእይታ ጥበብ አላባውያን አንድን ስነ-ሰዕል ለመሳል (ለመስራት) የሚያስፈልጉንን እና የሚጠቅሙንን ነገሮች በአግባቡ ተጠቅመን እንድንሰራ የሚረዳን ጽንሰ-ሃሳብ ነው፡ የእይታ ጥበብ አላባውያን በስነ-ጥበብ ስራ ላይ መሰረታዊ የሆኑ አጋዥ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚሳሉና የሚቀረጹ ሆነው ለተማሪዎች በተሻለና ግልጽ በሆነ መንገድ የቀረቡ ናቸው::

የእይታ ጥበብ አላባውያን ተብለው በዚሁ ክፍለ-ትምህርት የተካተቱት መስመር፣ ዝርግ ቅርጽ፣ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ጥቁረት/ንጣት፣ ለስላሳ/ሸካራ እንዲሁም መጠን እና ድግግሞሽ ናቸው::

## በዚህ የትምህርት ርእስ መጨረሻ

- ተማሪዎች ስለ መስመርና የመስመር አይነቶች ይረዳሉ
- ተማሪዎች ስለ ቅርጽና ዝርግ ቅርጽ አይነቶች ይረዳሉ

### የመወያያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ስለ መስመሮችና ቅርጾች ከዚህ በፊት የምታውቁትን እውቀት መሰረት አድርጋችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ::

## 1.1.1. መስመር

መስመር ማለት ከአንድ መነሻ ነጥብ ተነስተን ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች መጓዝ ማለት ነው፡፡ ነጥቦች በተከታታይ ሲደረደሩ ወይም በተመሳሳይ ረድፍ ሲቀመጡ የሚፈጠር የነጠብጣቦች ጥርቅም ውጤት ነው፡፡ መስመር ከእይታ ጥበብ አላባውያን አንዱ እና ዋነኛው ሲሆን ሁሉንም የእይታ ጥበባት መስራት ወይም መንደፍ ስንጀምር መስመርን እንጠቀማለን፡፡ መስመሮች ሸካራና/ለስላሳ፣ ጥቁረትና/ንጣት፣ ቀጭንና/ወፍራም እንዲሁም አጭርና/ረዥም መስመሮችን ልንፈጥር እንችላለን፡

### የመስመር አይነቶች

- አግድም መስመር
- ቋሚ መስመር
- ሰያፍ መስመር
- ደጋን መስመር
- ዚግዛግ መስመር
- ሞገዳማ መስመር

### አግድም መስመር

ከግራ ወደ ቀኝ እንዲሁም ከቀኝ ወደ ግራ የሚሰመር የመስመር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ 1.1፡-**



ምስል 1.1: አግድም መስመር

### ቋሚ መስመር

ከላይ ወደ ታች ወይም ከታች ወደ ላይ የሚሰመር የመስመር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ 1.2፡-**



ምስል 1.2: ቋሚ መስመር

### ሰያፍ መስመር

ከላይ ወደ ታች ወይም ከታች ወደ ላይ ጋደል ብሎ የሚሰመር የመስመር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ 1.3፡-**




ምስል 1.3: ሰያፍ መስመር

## ደጋን መስመር

በግማሽ ክብ የሚሰመር የመስመር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ 1.4፡-**



ምስል 1.4: ደጋን መስመር

## ዝግዛግ መስመር

ሁለት ሰያፍ መስመሮች በተለያየ አቅጣጫ ሲሰመሩ የሚፈጠር መስመር ነው፡፡

ምሳሌ1.5፡-




ምስል 1.5: ዝግዛግ መስመር

## ሞገዳማ መስመር

ሁለት የተለያዩ ደጋን መስመሮችን በተለያየ አቅጣጫ በማስመር የሚገኝ የመስመር አይነት ነው፡፡

**ምሳሌ 1.6፡-**



ምስል 1.6: ሞገዳማ መስመር

## ተጨማሪ የመስመር አይነቶች

መስመሮች በተለያየ ቅርጽ እና አይነት ሊሰመሩ ይችላሉ

**ምሳሌ 1.7፡-**



ምስል 1.7: የተለያዩ የመስመር አይነቶች

**መልመጃ 1.1**

1. ሁሉንም የመስመር አይነቶች እየሰራችሁ ተለማመዱ
2. አግድምና ቋሚ መስመሮችን አያይዛችሁ ስሩ
3. ደጋንና ስላሽ መስመሮችን አያይዛችሁ ስሩ

## 1.1.2. ዝርግ ቅርጽ


ዝርግ ቅርጽ ማለት መስመርን በመጠቀም የሚፈጠር ዝግ የሆነ ቦታ ነው። ዝርግ ቅርጽ ሁለት አውታረ መጠን ያለው ሲሆን እነዚህም ቁመትና ርዝመት ናቸው። የዝርግ ቅርጽ አይነቶች በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም፡-

- ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርጽ (ኦርጋኒክ ሼፕ)
- ሰው ሰራሽ ዝርግ ቅርጽ (ጂኦሜትሪካል ሼፕ)


### ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርጽ (ኦርጋኒክ ሼፕ)

በዚህ የዝርግ ቅርጽ ምድብ ውስጥ የተለያዩ በተፈጥሮ የምናገኛቸው የዝርግ ቅርጽ አይነቶች ይካተታሉ።

**ምሳሌ 1.8፡-**



ምስል 1.8: ቅጠል



ምስል 1.9: የሰው ምስል

### ሰው ሰራሽ ዝርግ ቅርጽ (ጂኦሜትካል ሼፕ)


በዚህ የዝርግ ቅርጽ ምድብ ውስጥ የምናገኛቸው ማስመሪያዎችን በመጠቀም የምንሰራቸው የዝርግ ቅርጽ አይነቶች ናቸው።

**ምሳሌ 1.9፡-**

- ክብ
- ሶስት ማዕዘን
- አራት ማዕዘን

### ክብ


ክብ ማለት ሁለት የደጋን መስመሮችን በመገጣጠም የምናገኘው የዝርግ ቅርጽ አይነት ነው፡፡



ምስል 1.10: ክብ

### ሶስት ማዕዘን

ሁለት ስላሽ መስመሮችንና አንድ አግዳሚ መስመርን በመገጣጠም የምናገኘው የዝርግ ቅርጽ አይነት ነው፡፡



ምስል 1.11: ሶስት ማዕዘን

### አራት ማዕዘን

ሁለት አግዳሚ መስመሮችንና ሁለት ቋሚ መስመሮችን በመገጣጠም የምናገኘው የዝርግ ቅርጽ አይነት ነው፡፡



ምስል 1.12: አራት ማዕዘን

### መልመጃ 1.2

1. ዝርግ ቅርፆችን ደጋግማችሁ ሳሉ
2. ሶስት ማዕዘን የሆኑ ዝርግ ቅርጾችን እየሳላችሁ ተለማመዱ
3. አራት ማዕዘን የሆኑ ዝርግ ቅርፆችን ስሩ
4. ክብ ዝርግ ቅርጾችን በተለያየ መጠን ሳሉ
5. ተፈጥሯዊ ዝርግ ክብ ቅርጾችን ስሩ
6. ሰው ሰራሽ አራት መአዘን ዝርግ ቅፆችን በመሳል ተለማምዱ
7. ሶስት ማዕዘንና ክብ ቅርጽ ያላቸውን ሥዕሎችሰርታችሁ አሳዩ
8. ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ እንዲሁም አራት ማዕዘንና ክብ ዝርግ ቅርጾችን በሰዕል ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

## 1.1.3. ቅርጽ

ቅርጽ ማለት ሶስት አውታረ-መጠን ያለው ማለትም ቁመት፣ርዝመት እና ጥልቀት ያለው የቅርጽ አይነት ነው፡፡ ሸካራና ለስላሳ፤ጥቁረትና ንጣት ያላቸውን የቀለም ቅብና ሌሎችም የእይታ ጥበባት ውጤቶችን ባለ ሶስት አውታረ-መጠን ቅርፆችን በመጠቀም መስራት ይቻላል፡፡

### የቅርጽ አይነቶች

- ተፈጥሯዊ ቅርጽ
- ሰው ሰራሽ ቅርጽ

### ሀ. ተፈጥሯዊ ቅርጽ

በዚህ የቅርጽ ምድብ ውስጥ የተለያዩ በተፈጥሮ የምናገኛቸው የቅርጽ አይነቶች ይካተታሉ፡፡




ምስል 1.13: ዛፍ



ምስል 1.14: ተራራ

### ለ. ሰው ሰራሽ ቅርጽ


በዚህ የዝርግ ቅርጽ ምድብ ውስጥ ማስመርያዎችን በመጠቀም የምንሰራቸው የዝርግ ቅርጽ አይነቶች ናቸው፡፡



ምስል 1.15: ኩብ



ምስል 1.16: ሲሊንደር




ምስል 1.17: የተለያዩ ሰው ሰራሽ ቅርጾች

**መልመጃ 1.3**

1. የቅርጽ አይነቶች በስንት ይከፈላሉ?
2. ቅርጽ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ተፈጥሯዊ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ስዕል ስላችሁ አሳዩ፡፡
4. የተፈጠሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርጾችን ምሳሌ ስጡ፡፡
5. በቤታችን የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶችን ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ ቅርጽ በሰዕል ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
6. አራት ማዕዘን ቅርጾች ምን ተብለው ይጠራሉ?

## 1.1.4. ቀለም


ቀለም ማለት ብርሃን በአንድ ቁስ ላይ አርፎ ሲንጸባረቅ በአይናችን ስናየው የምናገኘው ነገር ነው፡፡ ቀለምን የምናገኘው ብርሃን በፀሃይ ብርሃን አማካኝነት ተንጸባርቆ ወደ አይናችን ሲገባ ነው፡፡



ምስል 1.18: የቀለም አፈጣጠር ሂደት

### የቀለም አቀማመጥ (ከለር ዊል)

የቀለም አቀማመጥ ማለት አንዱ ቀለም ከሌላው ቀለም ያለውን ግንኙነትና ሲቀላቀሉ የሚሰጡትን አዲስ የቀለም አይነት የሚያሳይ የቀለማት አቀማመጥ ሂደት ነው፡፡ መሰራች ቀለማትን በመጠቀም እንደሚከተለው በስዕላዊ መግለጫ ተቀምጧል፡፡





ምስል 1.19: የቀለማት አቀማመጥ

የቀለም አይነቶች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነሱም :-

- የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት (መስራች ቀለማት)
- ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት
- ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት

## ሀ. የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት (መስራች ቀለማት)

የመጀመርያ ደረጃ ቀለማት (መስራች ቀለማት) የምንላቸው ከማንኛውም ቀለም ጋር ተደባልቀው የማናገኛቸው የቀለም አይነቶች ናቸው። እነዚህን የቀለም አይነቶች ከተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች ወይም ከአዝርዕቶች በመቀመም የሚዘጋጁ ናቸው። እነርሱም:-



## ለ. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት

ሁለት የተለያዩ የመጀመርያ ደረጃ ቀለማትን (መስራች ቀለማትን) በመቀላቀል የምናገኘው የቀለም አይነት ሁለተኛ ደረጃ የቀለም አይነት ይባላል፡፡ የመጀመርያ ደረጃ ቀለማትን (መስራች ቀለማትን) በመቀላቀል ሶስት የተለያዩ የቀለም አይነቶችን ማግኘት እንችላለን፡፡ እነርሱም፡-

አረንጓዴ

ብርቱካናማ

ወይንጠጅ

- ብርቱካናማ ቀለምን የምናገኘው ሁለት የመጀመርያ ደረጃ ቀለማትን (መስራች ቀለማትን) በእኩል መጠን በመቀላቀል ሲሆን ቀለሞችም ቀይ እና ቢጫን በማደባለቅ ነው፡፡
- አረንጓዴ ቀለምን ለመፍጠር ቢጫ ቀለምንና ሰማያዊ ቀለምን (ሁለቱም የመጀመሪያ ደረጃ ወይም መስራች ቀለማት ናቸው) እኩል በመደባለቅ ነው፡፡
- የወይን ጠጅ ቀለምን ሰማያዊና ቀይ ቀለምን (ሁለቱም የመጀመሪያ ደረጃ ወይም መስራች ቀለማት ናቸው) በእኩል መጠን በመደባለቅ እናገኛለን፡፡

### አንደኛ ደረጃ ቀለማትን በመቀላቀል የምናገኛቸው ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቀይ | + | ቢጫ | = | ብርቱካናማ |
| ቢጫ | + | ሰማያዊ | = | አረንጓዴ |
| ሰማያዊ | + | ቀይ | = | ወይን ጠጅ |

## ሐ. ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት

የሶስተኛ ደረጃ ቀለማትን የምናገኘው የመጀመርያ ደረጃ ቀለማትንና (መስራች ቀለማትንና) ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን አንድ ላይ በመደባለቅ ነው። እነዚህም ቀለማት እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቢጫ | + | ብርቱካናማ | = | ቢጫ ብርቱካናማ |
| ቀይ | + | ብርቱካናማ | = | ቀይ ብርቱካናማ |
| ቀይ | + | ወይን ጠጅ | = | ቀይማ ወይን ጠጅ |
| ሰማያዊ | | ወይን ጠጅ | | ሰማያዊ ወይን ጠጅ |
| ሰማያዊ | | አረንጓዴ | | ሰማያዊ አረንጓዴ |
| ቢጫ | | አረንጓዴ | | ቢጫማ አረንጓዴ |

ከላይ በተቀመጡት የቀለማት ማሳያ ሳጥን አናት ላይ ከ 1-3 የተሰጡት ቁጥሮች የመጀመሪያ ደረጃ ቀለምን (መስራች ቀለምን) ፣ ሁለተኛ ቀለምን እና ሶስተኛ ደረጃ ቀለምን በተከታታይ ያሳያሉ፡፡

## የቀለማት አቀማመጥ ቅደም ተከተል

- ሞቃት ቀለማት
- ተቀራራቢ ቀለማት
- ቀዝቃዛ ቀለማት
- ተቃራኒ ቀለማት

## ሀ. ሞቃት ቀለማት

እነዚህ ቀለማት ቀይ፣ብርቱካናማ እና ቢጫ እንዲሁም በመሃል ያሉትን ቀለማት ይወክላሉ፡፡

ቀይ ቀይ ብርቱካናማ ብርቱካናማ ቢጫ ብርቱካናማ ቢጫ




ምስል 1.20: ሞቃት ቀለማት

## ለ. ቀዝቃዛ ቀለማት

እነዚህ ቀለማት ሰማያዊ ፣ አረንጓዴ እና ወይንጠጅ ሆነው በመካከላቸው ሌሎች ቀለማትንም የሚያካትቱ ናቸው፡፡


አረንጓዴ ሰማያዊ አረንጓዴ ሰማያዊ ሰማያዊ ወይን ጠጅ ወይን ጠጅ



ምስል 1.21: ቀዝቃዛ ቀለማት

## ሐ. ተቃራኒ ቀለማት

እነዚህ የቀለማት አይነቶች በቀለም አቀማመጥ ቅደም ተከተል ላይ በትይዩ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ቢጫ እና ወይን ጠጅ




ምስል 1.22: ምስል 1.22 ተቃራኒ ቀለማት

## መ. ተቀራራቢ ቀለማት

እነዚህ የቀለም አይነቶች በቀለም አቀማመጥ ቅደም ተከተል ላይ ተቀራርበው የተቀመጡ ሶስት የቀለም አይነቶችን ይወክላሉ፡፡

**ምሳሌ፡-**

ቀይ - ቀይ ብርቱካን - ብርቱካን



ምስል 1.23: ተቀራራቢ ቀለማት

### መልመጃ 1.4


1. ቀለም ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቀለም አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
3. የመጀመርያ (መስራች) ቀለማት እነማን ናቸው?
4. ሶስተኛ ደረጃ ቀለማትን የምናገኘው በምን አይነት ዘዴ ነው?

5. ተቃራኒ ቀለማት የምንላቸው እነማን ናቸው?
6. ተቃራኒ ቀለማትን ቀብታችሁ አሳዩ።
7. ተከታታይ ቀለማት የምንላቸው የትኞቹን ቀለማት ነው?
8. የቀለማትን አቀማመጥ በተማራችሁት መሰረት በሥዕል ሰርታችሁ አሳዩ።


## 1.1.5. ጥቁረትና ንጣት

ጥቁረትና ንጣት ማለት የቀለማትን ደረጃ በጠበቀ መልኩ ከ ጥቁረት እስከ ንጣት ወይም ከንጣት ወደ ጥቁረት ያለውን የቀለም ደረጃ በቅብ ስራ የምንገልጽበት ነው። ጥቁረትና ንጣት ዘጠኝ የተለያዩ ደረጃዎች አሏቸው። ከጥቁር ወደ ነጭ ወይም ከነጭ ወደ ጥቁር ሊደረደሩ ይችላሉ። እነርሱም፦

1. ጥቁር
2. ከፍተኛ ጥቁር
3. ጨለማ
4. ዝቅተኛ ጨለማ
5. የነጭና የጥቁር መካከለኛ
6. 9. ነጭ
7. ከፍተኛ ብርሃን
8. ብርሃን
9. ዝቅተኛ ብርሃን




ወይም



1 2 3 4 5 6 7 8 9

ምስል 1.24: የጥቁረትና የንጣት ደረጃዎች


**መልመጃ 1.5**

1. ጥቁረትና ንጣት በስንት ይከፈላሉ?
2. ጥቁረትና ንጣት ስንል ምን ማለታችን ነው?
3. ጥቁረትና ንጣት ምን ለመስራት ያገለግላሉ?
4. ከጥቁር ወደ ነጭ ባለው ደረጃ ውስጥ አንደኛ፣አምስተኛ እና ዘጠነኛ ላይ ያሉትን ለይታችሁ ስሩ
5. ከ 1-9 ያሉትን የጥቁረትና ንጣት ደረጃዎችን በምስል አሳዩ

## 1.1.6. ለስላሳና ሸካራ

አንድን ቁስ በእጃችን ስንነካው የሚሰማን ስሜት እንዲሁም መንካት የማንችላቸውን በአይናችን አይተን የምንለየው ስሜት ነው፡፡ ሸካራ እና ለስላሳ ፣ ጠንካራና ስስ የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

**ምሳሌ ፡-**



ምስል 1.25፡ ልስላሴና ሸካራ


**መልመጃ 1.6**

1. ለስላሳና ሸካራ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ልስላሴና ሸካራነት በስንት ይከፈላል?
3. ለስላሳ የሆኑ ሥዕሎችን ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
4. ሸካራ የሆኑ ሥዕሎችን ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

## 1.1.7. ድግግሞሽ

ድግግሞሽ ከእይታ ጥበብ አላባውያን ውስጥ አንዱ ሲሆን የተለያዩ መስመሮችን፣ ዝርግ ቅርጾችን፣ ቅርጾችን፣ ቀለማትን እና ሌሎችንም በመጠቀም አንድን ስነ-ሥዕል ከ አንድ ጊዜ በላይ ደጋግመን የምንሰራበት የጥበብ አይነት ነው።

**ምሳሌ ፡-**




ምስል 1.26: ድግግሞሽ

**መልመጃ 7**

1. ድግግሞሽ ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. ድግግሞሽን በዝርግ ቅርጽ ሰርታችሁ አሳዩ።
3. ድግግሞሽ ያላቸውን ተፈጠሯዊ ምስሎች በሥዕል አሳዩ።

## 1.1.8. መጠን

መጠን ማለት ሁለት የተለያዩ ምስሎችን በቁመታቸው ወይንም በቀለማቸው መጠን ለይተን የምናስቀምጥበት የጥበብ አይነት ነው።




ምስል 1.27: መጠን

**መልመጃ 1. 8**

1. የመጠንን ጽንሰ-ሀሳብ አብራሩ፡፡
2. የተለያየ መጠን ያላቸውን በቤታችን የምንገለገልባቸውን የሁለት እቃዎች ሥዕል ሰርታችሁ አሳዩ

## 1.2. የሙዚቃ አላባውያን

### መግቢያ

ምት በሙዚቃ ውስጥ ያለ የድምጽ እና የዝምታ (እረፍት) ድግግሞሽ ሲሆን በሙዚቃ የንድፈ-ሀሳብ ትምህርት ውስጥ የሙዚቃ ኖታዎች እና የዝምታ (የእረፍት) ምልክቶች በተወሰነ የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ ተከታትለው እና ደጋግመው የመምጣት ሂደትን ብሎም የሚፈጥሩትን ሙዚቃዊ የድምጽ ፍሰት ያሳያል፡፡ ተማሪዎችን ለበለጠ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የኖታዎች የጊዜ ቆይታን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

### በዚህ የትምህርት ርእስ መጨረሻ

- ተማሪዎች የኖታዎች ስያሜና የቆይታ ግዜያቸውን እስከ አንድ ስምንተኛ የኖታ አይነቶች ይረዳሉ
- ተማሪዎች የእረፍት ምልክቶችን ስያሜና የቆይታ ግዜያቸውን እስከ አንድ ስምንተኛ የእረፍት አይነቶች ይረዳሉ

## የመወያያ ጥያቄ

- ተማሪዎች በአራተኛ ክፍል ቆይታችሁ የተማራችኋቸውን የኖታ እና የእረፍት ምልክት አይነቶች በመለየት ተወያዩባቸው፡፡

## 1.2.1. ምት (ሪትም)

ሰንጠረዥ 1.1: የኖታዎች ስያሜና የቆይታ ግዜ (አጨዋወታቸው)


| የኖታው ስም | የኖታ ቅርፅ | አጨዋወት |
|---|---|---|
| ሙሉ ኖታ | 𝅝 | 4 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ መጫወት |
| ግማሽ ኖታ | 𝅗𝅥 | 2 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ መጫወት |
| ሩብ ኖታ | ♩ | 1 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ መጫወት |
| 1/8 ኖታ | ♪ | ግማሽ ምት ድምጽ ሳያቋርጥ መጫወት |

ሰንጠረዥ 1.2: የዕረፍት ምልክቶች ስያሜና የቆይታ ግዜ (አጨዋወታቸው)


| የኖታው ስም | የኖታ ቅርፅ | አጨዋወት |
|---|---|---|
| ሙሉ የዕረፍት ምልክት | 𝄻 | 4 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ ምቱን ተከትሎ ማረፍ |
| ግማሽ የዕረፍት ምልክት | 𝄼 | 2 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ ምቱን ተከትሎ ማረፍ |
| ሩብ የዕረፍት ምልክት | 𝄽 | 1 ምት ድምጽ ሳያቋርጥ ምቱን ተከትሎ ማረፍ |
| 1/8 የዕረፍት ምልክት | 𝄾 | ግማሽ ምት ድምጽ ሳያቋርጥ ምቱን ተከትሎ ማረፍ |

### የኖታ ምልክቶች ፒራሚድ

የኖታ ፒራሚዶች የሚያሳዩት የኖታ ዋጋ ክፍልፋዮችን ነው፡፡




**የኖታ ዋጋ ክፍልፋዮች**



የኖታ ምልክቶች ፒራሚድ


ከላይ ያሉትን የኖታ ፒራሚዶች በቁጥር ዋጋቸው ተክተን እንደሚከተለው ማስቀመጥ እንችላለን




የእረፍት ምልክቶች ዛፍ

ከላይ በኖታ ምልክቶች ላይ የተጠቀሰው የቁጥር ዋጋ ለተከታዩ የእረፍት ምልክት ክፍልፋይም ይሰራል፡፡ ስለዚህ ከላይ ያለው የእረፍት ምልክት 4 ሲይዝ ከስር በየደረጃው ያሉት በግማሽ እያነሱ ይሄዳሉ፡፡

## የእረፍት ምልክት ክፍልፋዮች




### መልመጃ 1.9

የኖታና የእረፍት ምልክቶች ሂሳብ


1. የሚከተሉትን የኖታና የእረፍት ምልክቶች ዋጋ በመደመር ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታ ዋጋ በቁጥር በባዶው ቦታ ላይ ሙሉ፡፡



2. የኖታዎችን ዋጋ ባዶ ሳጥን ውስጥ በቁጥር አስቀምጡ



3. የኖታዎችን ዋጋ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በቁጥር አስቀምጡ



## 1.2.2. የድምጽ ከፍታ/ዝቅታ (ዳይናሚክስ)

የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) የሙዚቃ ለስለስና ጮክ ማለት ሲሆን በሌላ አባባል የሙዚቃ ድምጽ መጠን ማለት ነው። የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) የሙዚቃ ደራሲዎች ወይም ዘፋኞች ሙዚቃው ትርጉም እንዲኖረው ወይም ጥራቱን እንዲጠብቅ ልዩ ትኩረት ከሚሰጡት የሙዚቃ መሰረታዊ ክፍል አንዱ ነው። በመሰረቱ ድምፅ ከመጠን በላይ እንዲጮህ ከተደረገ በጤና ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል። አካባቢያችንም በድምፅ ሊበከል ይችላል። ይህ እንዳይከሰት የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡ ፡ በአውሮፓውያን የሙዚቃ ባህል አጻጻፍ የሙዚቃውን መለስለስና መጮህ ማለትም የድምፅ ከፍና (ጮክ ማለት) ዝቅ ማለት (መለስለስ) የሚያሳዩ ምልክቶች ይገኛሉ።

የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) ሕጎች የሙዚቃ ድምጽ ለስለስ ወይም ጎላ ለማድርግ የምንጠቀምበት ምልክት ነው። እንደዜማው የአደራረስ አይነት ጣዕም ለመስጠት ሲባል የተለያዩ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) ዓይነቶች ኖታው በሚያርፍበት ሥር ወይም ላይ እንዲሰፍሩ ይደረጋል። በዚህ ክፍል ደረጃ በጣም መሠረታዊ ናቸው ተብለው ተግባራዊ ሊሆኑ የሚገባቸው የዳይናሚክስ ምልክቶች ቀጥለው ይቀርባሉ።

ሰንጠረዥ 1.3: ሰንጠረዥ 1.3 የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) ዓይነቶች እና ትርጉማቸው

| የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) ዓይነቶች በማሳጠር | ዓለም አቀፍ መጠሪያው | ትርጉም |
|---|---|---|
| P | ፒያኖ | በዝቅተኛ/ለስለስ ባለሁኔታ ዘምሩ (ተጫወቱ) |
| P P | ፒያኖ ሲሞ | በጣም በዝቅተኛ/ለስለስ ባለሁኔታ ዘምሩ (ተጫወቱ) |
| F | ፎርቴ | በከፍተኛ ድምጽ ዘመሩ (ተጫወቱ) |
| f f | ፎርቴ ሲሞ | በጣም በከፍተኛ ድምጽ ዘምሩ (ተጫወቱ) |

## መልመጃ 10

1. የሚከተሉትን የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) ምልክቶች ከትክክለኛው ትርጉማቸው ጋር መስመር በመስራት አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| FF | በከፍተኛ ድምጽ ዘምሩ (ተጫወቱ) |
| F | በጣም በዝቅተኛ/ለስለስ ባለ ሁኔታ ዘምሩ (ተጫወቱ) |
| P | በጣም በከፍተኛ ድምጽ ዘምሩ (ተጫወቱ) |
| pp | በዝቅተኛ/ለስለስ ባለሁኔታ ዘምሩ (ተጫወቱ) |

## 1.2.3. የድምጽ ፍጥነትና እርጋታ (ቴምፖ)

የሙዚቃ ፍጥነቱ ሜትሮኖም በሚባል የጊዜ / የፍጥነት/ መለኪያ የተወሰነ ክልል ያለው ሲሆን ሙዚቃ ሲጻፍ የሙዚቃ ደራሲያን በሚጽፏቸው ድርሰቶች መጀመሪያ አመልካች ቁጥርን አብረው ይጽፋሉ፡፡ ይህም ማለት በተሰጠው የቁጥር መጠን ወይም ፍጥነት ሙዚቃውን የሚጫወተው ሰው እንዲተገብረው ለማስገንዘብ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 1.4: የድምጽ ፍጥነትና እርጋታ (ቴምፖ) ዓይነቶች እና ትርጉማቸው

| ስም | አጠቃቀሙ |
|---|---|
| አዳጆ | በጣም ቀስ ያለ ጐተት እያረገ በመቁጠር የሚሠራ ሙዚቃ |
| አንዳንቴ | መካከለኛ በጣም ያልፈጠነ በሰው እርምጃ መጠን እየተቆጠረ የሚሄድ የሙዚቃ ፍጥነት ሲሆን ፍጥነቱ ዝግተኛ ነዉ |
| ሞደራቶ | የማይፈጥን የማይጐተት መካከለኛ ፍጥነት |
| አሌግሮ | ፈጠን ያለ |
| ኘሬስቶ | በጣም ፈጣን የሆነ የሙዚቃ አቆጣጠር |

## መልመጃ 1.11

የጎደሉ ቦታዎችን በትክክለኛ መልሶቻቸው አሟሉ፡፡

| ስም | አጠቃቀሙ |
|---|---|
| አዳጆ | |

| | |
|---|---|
| | መካከለኛ በጣም ያልፈጠነ በሰው እርምጃ መጠን እየተቆጠረ የሚሄድ የሙዚቃ ፍጥነት ሲሆን ዝግተኛ ነዉ. |
| ሞደራቶ | |
| አሌግሮ | ፈጠን ያለ |
| ኘሬስቶ | |

## 1.2.4. የድምጽ መወፈር/መቅጠን/መካከለኛ መሆን (ፒች)

የድምጽ መወፈር/መቅጠን/መካከለኛ መሆን (ፒች) የድምጽን (የሰው ድምጽም ሆነ የሙዚቃ መሳርያ ድምጽ) የመወፈር፣የመቅጠን ወይም መካከለኛ የመሆን ባህሪን የሚገልጽ ሲሆን የሰው ልጅ ድምጽንም ሆነ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የድምጽ መወፈር፣መቅጠን ብሎም መካከለኛ መሆን የሚወሰነው በድምጹ እርግብግቢት (ፍሪኩየንሲ) ነው፡፡ እርግብግቢት (ፍሪክዌንሲ) የሚለካው (ኸርዝ ወይም Hz) ነው፡፡ አንድ ኸርዝ አንድ እርግብግቢት በሰከንድ የሚይዘውን ያመላክታል፡፡ ስለ ኸርዝ የበለጠ ለመረዳት የፊዚክስ መምህራንን መጠየቅ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ፈጣን የድምፅ እርግብግቢት ቀጭን ድምጽን የሚፈጥር ሲሆን ዝቅተኛ የድምፅ እርግብግቢት ደግሞ ወፍራም ድምጽን የሚፈጥር ይሆናል፡፡

### መልመጃ 1.12

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ትክክል የሆነው ሃሳብ ለዩ
   ሀ. የሴት ልጅ ድምጽ ከወንድ ልጅ ድምጽ ይወፍራል
   ለ. የወንድ ልጅ ድምጽ ከሴት ልጅ ድምጽ ይቀጥናል
   ለ. የሴት ልጅ ድምጽ ከወንድ ልጅ ድምጽ ይቀጥናል
2. ፈጣን የድምፅ እርግብግቢት ቀጭን ድምጽን ይፈጥራል
   ሀ) እውነት ለ) ሀሰት
3. ዝቅተኛ የድምፅ እርግብግቢት ወፍራም ድምጽን ይፈጥራል
   ሀ) እውነት ለ) ሀሰት

### ውዝዋዜ

ከውዝዋዜ ቢያንስ አምስት መሰረታዊ ጥቅሞችን እንደምታገኙ ይታመናል፡፡ እነዚህም፡-

- አካላዊ ጤናን ማግኘት
- ስሜታዊ እድገትን ማገዝ
- የማህበራዊ ህይወት ክህሎትን መጨመር

☆ ፈጠራን ማበረታታት

〆 የእውቀት እድገትን ማገዝ

**መልመጃ 1.13**

4. የምታውቋቸውን የውዝዋዜ አይነቶች በሚገባ በመለማመድ በክፍል ውስጥ አቅርቡ
5. አዲስ እና ቀላል የውዝዋዜ አይነት በቡድን ሆናችሁ በመፍጠር በክፍል ውስጥ አቅርቡ

## 1.3. መሰረታዊ የመድረክ ተውኔት ጥበብ (ቴአትር) አላባውያን

### መግቢያ

ቴአትር በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ቀጥታ ተመልካች ከመድረሱ በፊት የእውነተኛ ወይም ምናባዊ ክስተት ልምድን ለማቅረብ የቀጥታ ተዋንያንን የሚጠቀም የጥበብ የትብብር ቅጽ ነው። ተዋንያን በምልክት ፣ በንግግር ፣ በዘፈን ፣ በሙዚቃ ወይም በዳንስ ጥምረት ይህንን ተሞክሮ ለተመልካቾች ሊያሳውቁ ይችላሉ። ቴአትርን ቴአትር ሊያስብሉ የሚችሉ አስፈላጊ አካላት አሉ። ቴአትር ከትውን ጥበባት ዘርፎች ውስጥ የሚካተት የእይታ ጥበብ ዘርፍ ነው። የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚከወን ታሪክ ነው።

### በዚህ የትምህርት ርእስ መጨረሻ

- ተማሪዎች የተውኔት ድርሰት አላባውያንን ይረዳሉ።

**የመወያያ ጥያቄ**

〆 ተማሪዎች ስለ ቴአትር ጥበብ ከዚህ በፊት የምታውቋቸውን ሀሳቦች ተወያዩባቸው።

### ተዋናይ

ተዋናይ ስንል ለብቻው አንድን ገፀ-ባህሪ የሚጫወት ሲሆን ተዋንያን ደግሞ በቡድን ተውኔት የሚያቀርቡ ሰዎችን ለመግለጽ ነው። የተውኔቱን ታሪክ በቃላቸው፣ በድርጊታቸው፣ ለተመልካች የማስተላለፍ ተልእኮ ያላቸው ናቸው። የእጅ ምልክቶች፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች እና ምልክቶች ለተለያዩ ገጸ -ባህሪዎች ውበትን ይሰጣል። በእያንዳንዱ ተውኔት ውስጥ ቢያንስ አንድ ተዋናይ አለ። ብዙውን ጊዜ በቴአትር ውስጥ ከአንድ በላይ ተዋንያን አሉ። ሆኖም አንድ ተውኔት ከሰዎች በተጨማሪ እንዲሁ

በአሻንጉሊቶች ሊዳብር እንደሚችል ማሳየት ይቻላል። እንደነዚህ አይነት ተውኔቶች ለህፃናት ተመራጭ አቀራረብ ዘዴ ነው።

ድምጹ ወደ ሁሉም ታዳሚዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና ለገጸ-ባህሪው ሀይል ለመስጠት ተዋንያን ድምፃቸው ብዙውን ጊዜ ኃይለኛ በሆነ ድምጽ እና በመጠኑን ከፍተኛ በማድረግ ሊተውኑ ይችላሉ። ሁለቱም የቃል እና የንግግር ቋንቋዎች በታሪኩ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ታሪኩን ለተመልካቾች በጥሩ ሁኔታ እንዲረዱት ለማድረግ ተዋንያን ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

## ጽሑፈ-ተውኔት (ድርሰት)

ከቴአትር አላባውያን መካከል አንዱና ዋነኛው ድርሰት ነው። ጽሑፉ በሲኒማ ውስጥ ወይም በመድረክ ላይ በሚዘጋጅበት ጊዜ ድርሰት (ስክሪፕት) ተብሎ ይጠራል። ድርሰት ታሪኩን በሙሉ የያዘ እና የሚያብራራ ሲሆን ይህም በገቢር እና በትዕይንቶች የተዋቀረ ነው። ይህም ማለት በድርሰት ውስጥ ያለን ሴራ ያጠቃልላል። ያለ ድርሰት ትያትር መስራትም ሆነ ማቅረብ አይቻልም። ስለሆነም ድርሰት ለትያትር በጣም አስፈላጊዉ ክፍል ነው።

## አልባሳት

አልባሳት ስንል ተዋናዮች ወይም አሻንጉሊቶች የሚለብሷቸውን አልባሳት እና መለዋወጫዎችን ያካትታሉ። አልባሳት በተውኔት ዉስጥ ያሉትን ገጸ-ባህሪያት እድሜያቸዉን አኗኗራቸዉን ወዘተ የሚገልጽ ነዉ። በተጨማሪም አልባሳት ታሪኩ የሚከናወንበትን ጊዜ እና ቦታ ለመለየት ያስችለናል። ይህም ማለት አልባሳት ለተመልካቾች ብዙ መረጃዎችን ይሰጣል።

## የገፅ ቅብ (ሜካፕ)

የገፅ ቅብ (ሜካፕ) ሌላኛው የቴአትር አንድ አካል ነው። ይህም ተዋናዩ በተጠቀመው ሜካፕ አማካኝነት ተዋናዩን በአካላዊ ቁመናው (በተለይም በፊቱ) በኩል እንዲለይ ያስችለዋል። የገፅ ቅብ (ሜካፕ) እንደ ተዋናዩ ሁኔታ ወይም ዓይነት የሚወሰን ሆኖ የተዋንያንን ጉድለቶች ለመሙላት፣ለማጉላት እንዲሁም ለመደበቅ ያገለግላል። የገፅ ቅብ (ሜካፕ) በዋነኝነት የሚከናወነው በመዋቢያ ምርቶች፣ቀለሞች ወይም ክሬሞች ነው። ሜካፕ ባህሪያትን ከማሻሻል ወይም ከማጉላት በተጨማሪ ቁስሎችን፣ጠባሳዎችን፣ማድያት፣ጠቃጠቆዎችን ለማስመሰል ያስችላል።

## መብራት

የቴአትር ብርሃን ወይም መብራት ተዋናዮቹ መድረክ ላይ በሚወጡበት ጊዜ ለተመልካቾች በደንብ ለማሳየት የሚያግዝ ብርሃን ነው። ትያትሩ በሚሰራበት ወቅት ጥቅም ላይ

የሚወሉትን ሁሉንም መብራቶች እና ስፖትላይቶች ያካትታል። ስለዚህ የተወሰኑ ስሜቶችን ለማስተላለፍ ፣ ተዋንያንን ለማጉላት ፣ ለመደበቅ ወይም ቀን፣ማታ ፣ ሌሊት መሆኑን የምገልጽበት አንዱ መንገድ መብራቶችን በመጠቀም ነዉ።

## ግብዓተ-ድምጽ

ግብዓተ-ድምጽ በዋነኝነት ሙዚቃን እና የተለያዩ የድምፅ ውጤቶችን በቴአትር ውስጥ በማስገባት የምንጠቀምበት መንገድ ነው። ለምሳሌ በጥዋት ትዕይንት ውስጥ የወፎችን ድምጽ ቀርጸን አምጥተን ለተመልካቾች ልናሰማ እንችላለን። ታሪክን አፅንዖት ለመስጠት እና ለማበልጸግ የተለያዩ ድምፆችን ስንጠቀም ተውኔቱ የተሟላ ይሆናል። በተውኔቱ ውስጥ ልዩ ልዩ ድባቦችን ለመግልፅ ድምጽ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ለምሳሌ የከባድ መሳሪያ የተኩስ ድምፆችን መድረክ ላይ ለመጠቀም ሥለማንችል በድምጽ ብቻ ቀርጸን በድምጽ ማጉያ መሳሪያ በመጠቀም ልናሰማ እንችላለን።

## ዳይሬክተር

ዳይሬክተር ማለት በቴአትር ውስጥ የሚሳተፉ አካላት በሙሉ በትክክል እንዲሠሩ ቴአትሩን የሚያስተባብረው ሰው ነው። አስፈላጊ ከሆነ ዳይሬክተሩ በቴአትሩ ውስጥ ተዋናይ ሊሆን ይችላል። የዳይሬክተር ዋና ሥራ ትዕይንቶችን፣ተዋንያንን ፣ግባተ-ድምጽን፣የገፀ ቅብን፣መብራትን ወዘተ ማስተባበርን ያጠቃልላል። ቴአትሩን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በስኬት ለማጠናቀቅ ትልቅ ኃላፊነት ያለው ሰው ነው። በዚህም የተነሳ ዳይሬክተር የትያትሩ የጀርባ አጥንት ነዉ የሚባለው ለዚህ ነው።

## መድረክ እና ሲን (ትዕይንት)

መድረክ እና ሲን ታሪኩን ለማዘጋጀት የሚያገለገሉ የተለያዩ ማስጌጫዎችን ያጠቃልላል። ይህም ማለት ተዋናዮቹ የሚያቀርቡበትን መድረክ ከቴአትሩ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ቁሳቁሶች ያስጌጣል ማለት ነው። መድረክ እና ሲን ዓላማው ታሪኩ የተሰራበትን ዘመን፣ቦታ፣እንዲሁም የሚከናወንበትን ሁኔታ፣በትክክል ለተመልካቾትች ለማሳየት ትልቅ ድርሻ አለው።

## ተመልካች (ታዳሚ)

ታዳሚው ወይም ተመልካች ማለትም ተውኔቱን ወይም ቴአትሩን ለማየት በቦታው የሚገኙ ሰዎች ናቸው። የቴአትሩ ዓላማ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ሃሳቦችን በማንሳት በተለያዩ መንገዶች ለማዝናናት እና ቁምነገር ለማስጨበጥ ነው። ታዳሚዎችም ማህበራዊ ሁኔታዎችን በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ታሪካዊ ክስተቶችን በማየት፣በማስመሰል እና በማንጸባረቅ ግንዛቤዎችን እንዲጨብጡ ያግዛል። ቴአትር ታዳሚዎች የሚያዩትን ተውኔት በራሳቸው መንገድ ምላሽ መስጠት ይችላሉ።

### ቁሳቁሶች

ቁሳቁሶች ተዋናዮች በቴአትር ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ናቸው:: በድርጊቱ ላይ መሰረት ሊያንቀሳቅሷቸው ፣ ሊጥሏቸው ፣ ሊደብቋቸው ፣ ወዘተ የሚችሏቸው ልዩ ልዩ እቃዎች ናቸው:: እነዚህ ቁሳቁሶች የመድረክና ሲን አካል ሲሆኑ የቴአትሩ ልዩ ክፍሎች ናቸዉ::

### ኬሪዮግራፊ (ውዝዋዜዎች)

ውዝዋዜ ፣ ዳንስ እንዲሁም እንቅስቃሴዎች በቴአትር ውስጥ የተለመዱ ነገሮች ናቸው:: ተውኔቱን መሰረት በማድረግ የሚታዩትን ውዝዋዜዎችን ወይም ግጭቶችን ያካትታል:: የተዋንያን እንቅስቃሴዎች እና ጭፈራዎች በሙዚቃው እና በታሪኩ ላይ መሠረት በማድረግ ይከናወናሉ::

**መልመጃ 1.14**

እውነት ሐሰት በማለት መልሱ

1. የቲያትር አካላት በሙሉ በትክክል እንዲሠሩ የሚያስተባብረው ዳይሬክተር ነው፡
2. ግብዓተ-ድምጽ ታሪክን አፅንዖት ለመስጠት እና ለማበልጸግ ያስችለናል::

## 1.4. ቀላል የተንቀሳቃሽ ምስል መቅረጫ ዘዴዎች

ተንቀሳቃሽ ምስል (ቪዲዮ) የምንለው በአንድ ፍሬም ውስጥ የተነሱ ምስሎች ተሰብስበው ሲንቀሳቀሱ ተንቀሳቃሽ ምስልን ይፈጥራሉ:: ቪዲዮ የበርካታ ፎቶዎች በፍጥነት ተነስተው ሲንቀሳቀሱ ቪዲዮን ወይም ተንቀሳቃሽ ምስልን ይፈጥራሉ::

ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ለመቅረፅ ካሜራ ወይም የእጅ ስማርት ስልክ ሊኖረን ይገባል:: በመቀጠልም የምንቀርፅበትን ካሜራ ወይም የእጅ ስልክ መክፈትና ለቀረፃ ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋ::

የምንቀርፀውን ምስል ለምሳሌ ቃለ-ምልልስ ፣ ተፈጥሮ ፣ ፊልም ወዘተ. መሆኑን ለይተን ካወቅን በኋላ እና ጥቅሙን ከተረዳን በኋላ ተንቀሳቃሽ ምስሉን በካሜራችን ማስቀረት እንችላለን::

ሌላው የቀረፃ አይነቶችን ማወቅ ነው:: ይህም ማለት አንድን ምስል ለመቅረፅ ከመነሳታችን በፊት ምስሉን የምንቀርፀው ከላይ ወደ ታች ነው ወይስ ከታች ወደ ላይ ነው የሚለውን መለየት:: ሌላው ምስሉን የምንቀርፀው የምንቀርፀውን ቁስ ወይም ሰው ለማግዘፍ እና ትኩረትን እንዲስብ ለማድረግ ነው ወይስ አካባቢንና ቦታን (ለምሳሌ:- ከተማን ፣ የእግር

ኳስ ጨዋታን የመሳሰሉትን) ለማሳየት ነው የሚለውን መለየት ያስፈልጋል፡፡

የቀረፃ አይነቶች በባህሪያቸው የተለያዩ አይነቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

- ከወገብ በላይ
- በጣም አቅርበን
- ከአንገት በላይ
- በጣም አርቀን
- ሙሉ የሰው አቋምን አስገብተን የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የቀረፃ አይነቶችን ለተለያየ ሁኔታ ልንጠቀማቸው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡- አንድን ሰው በካሜራ እየቀረፅን ያደረገውን ስአት ወይም ከሰውነት ክፍሉ ውስጥ አይኑ ላይ ማተኮር ከፈለግን በጣም አቅርበን መቀረፅ ይኖርብናል ማለት ሲሆን የተናደደ ሰውን እንዲሁም ያዘነን ሰው መቀረፅ ከፈለግን ስሜቱን ከፊቱ ላይ ለማግኘት አቅርበን መቀረፅ ይኖርብናል፡፡ በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ ሰዎችን ለመቀረፅ ደግሞ ሙሉ አቋማቸውን በካሜራ እይታ ውስጥ በማስገባት እንቅስቃሴያቸውን ማሳየት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

ሌላው ተማሪዎች ማወቅ ያለባችሁ አይናችን ለማየት ብርሃን እንደሚያስፈልገው ሁሉ ካሜራችንም ምስል ለመቀረፅ ብርሃን ያስፈልገዋል፡፡ ካሜራችንንም ሳንንቀጠቀጥ በመያዝ በትክክለኛ አቋቋም ላይ በመሆን መቀረፅ የተሻለ ጥራት ያለው ምስል ማግኘት እንድንችል ይረዳናል፡፡

☆ የተግባር ስራ

- ተማሪዎች በቡድን በመሆን እና የመምህራችሁን የእጅ ስልክ ካሜራ በመጠቀም የ20 ሰከንድ ምስል የተማራችኋቸውን ዘዴዎች በመጠቀም ቀርፃችሁ በክፍል ውስጥ ስለሰራችሁት ስራ ውይይት አድርጉ፡፡
- የተናደደን ሰው ለመቀረፅ የምንጠቀመው የአቀራረፅ ዘዴ የቱ እንደሆነ ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ምላሹን አቅርቡ፡፡

## ማጠቃለያ


ይህንን ክፍለ-ትምህርት ለማጠቃለል እንዲረዳን የሚከተሉትን በስፋት ያየናቸውን ጽነሰ-ሀሳቦች አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል፡፡ የእይታ ጥበብ አላባውያን የሚባሉት መስመር፣ዝርግ ቅርጽ ፣ ቅርጽ ፣ ቀለም ፣ ጥቁረት/ንጣት፣ ለስላሳ/ሸካራ፣መጠንና ድግግሞሽ ናቸው፡፡ መስመር ማለት ከአንድ መነሻ ነጥብ ጀምሮ ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚሄድ ነው፡፡ ዝርግ ቅርጽ ማለት ሁለት አውታረ-መጠን ያለው ዝግ መስመር ማለት ሲሆን ቅርጽ ማለት ደግሞ ሶስት አውታረ-መጠን ያለው መስመር መሆኑን ለማየት ሞክረናል፡፡ ቀለም ስንል አንድ ቁስ ላይ ብርሃን ካረፈ በኋላ ወደ

አይናችን ተመልሶ የሚመጣው ነጸብራቅ ነው። ሌላው በዚህ ክፍለ-ትምህርት ለማየት የሞከርነው ጥቁረት/ንጣት ሲሆን ከንጣት ወደ ጥቁረትም ሆነ ከጥቁረት ወደ ንጣት ያሉ ደረጃዎችንም እንዲሁ ለመረዳት ሞክረናል። ለስላሳ/ሸካራ የሚለው ጽንሰ-ሀሳብም በዚሁ ክፍለ-ትምህርት በስፋት ያየነው ንዑስ ክፍለ-ትምህርት ነው። አንድን ቁስ በቀላሉ በማየትም ሆነ በመዳሰስ ልስላሴንና ሸካራነትን የምንለይበት ሂደት ነው። በመጨረሻም በእይታ ጥበብ አላባውያን ውስጥ መጠን ብሎም ድግግሞሽ የሚሉትን ሁለት ጭብጦች ተረድተናል።

ትውን ጥበባትን በተመለከተ ከሙዚቃ ጥበብ ጋር ተያይዞ ምት (ሪትም) ፣ የድምጽ ፍጥነትና እርጋታ (ቴምፖ) ፣ የድምጽ መቅጠን ፣ መወፈር እንዲሁም መካከለኛ መሆን (ፒች) ፣ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ (ዳይናሚክስ) የመሳሰሉትን ሀሳቦች በዝርዝር አንስተን ተወያይተናል። አልፎ ተርፎም የኖታዎች እና የእረፍት ምልቶችን በመጠኑ ተዋውቀናል። ሌላው የትውን ጥበብ አካል የሆነው ውዝዋዜ እንደመሆኑ መጠን ስለ ውዝዋዜ ጠቃሚ ሀሳቦች ተካተው ቀርበዋል። የመድረክ ቴአትርም የዚህ ክፍለ-ትምህርት አካል እንደመሆኑ መጠን  ለማካተት ተሞክሯል።

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ክፍልፋዮቹን አሟሉ (ጥያቄ ምልክቶቹን በትክክለኛ ምልክቶች ተኩ)




2. መስመር ፣ ዝርግ ቅርጽ ፣ ቅርጽ ፣ መጠን እና ድግግሞሽን ለእያንዳንዱ አንዳንድ ምሳሌ በመስጠት አሳዩ
3. ስለ ጥቁረትና ንጣት እንዲሁም ልስላሴና ሸካራነት ያላችሁን ግንዛቤ ለመምህሩ አስረዱ
4. ግብዓተ-ድምጽ ታሪክን አፅንዖት ለመስጠት እና ለማበልጸግ ያስችለናል።

   ሀ) እውነት                                  ለ) ሐሰት

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ፈጠራዊ አገላለጽ

### መግቢያ

ኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ በአምስተኛው መቶ ክፍለ-ዘመን በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት የተደረሱ የሙዚቃ ምልክቶች አሏት፡፡ የአውሮፓ ሀገራት ዘግይተውም ቢሆን ከኢትዮጵያ በኋላ የራሳቸውን የሙዚቃ አጻጻፍ ዘዴ ፈጥረዋል፡፡ የሃገራችንን የሙዚቃ ምልክቶች በስፋት የምትጠቀመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ስለሆነች የአውሮፓውያንን ምልክቶች ለሙዚቃ ትምህርት አገልግሎት ለመጠቀም እንገደዳለን፡ እነዚህን የአውሮፓውያን ምልክቶች በቦታና በጊዜ ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡ የጊዜ ምልክቶች የሚባሉት ጊዜውን የሚያሳዩን ሲሆኑ የቦታ የሚባሉት ደግሞ ቃናውን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ የጊዜ ምልክቶች የጨዋታና የዝምታ (የእረፍት) በመባል በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ የኖታ ምልክቶችና የእረፍት ምልክቶች የየራሳቸው ዋጋና የአቆጣጠር ስልት ያላቸው ሲሆን ሂሳባዊ ባህሪም አላቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍለ-ትምህርት የኖታና የእረፍት ምልክቶችን ተማሪዎች ትተዋወቃላችሁ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶችን እንዲሁም ሂሳባዊ ባህሪያቸውን ትረዳላችሁ፡፡ እንደዚሁም በተለያየ መንገድ ዋጋቸውን ትቆጥራላችሁ፡፡ ሌላው በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥ የተካተተው ጽንሰ-ሀሳብ የሶልፌጅ (ዶ ሬ ሚ...) የመዘመር ክህሎት ነው፡፡ ጆሮን በማሰልጠን በጥሩ ድምጽ በመዘመር የዝማሬ ክህሎታችንን እናዳብርበታለን፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተካተተው የባለ ቀለም ወረቀቶች እና የህትመት ስራ የእይታ ጥበባት አካል ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የተለያየ የአሰራር ዘዴ አላቸው፡፡ እነዚህም የባለ ቀለም ወረቀት (ሞዛይክ) በተፈጥሮም ሆነ በአካባቢያችን የምናያቸውን ነገሮች ወደ እይታ ጥበብ በመቀየር የምንፈልገውን ስዕሎች ከሰራን በኋላ እንደየ ሥዕሉ ቅርፅ እና መጠን በመቆራረጥ በባለ ቀለም ወረቀት (ሞዛይክ) የአሰራር ዘዴ መስራት ይቻላል፡፡ የድንች ህትመት የምንሰራባቸው የስዕሎች አንድን መልእክት በቀላሉ ለማስተላለፍ የሚመቹ

ናቸው። አሰራራቸውም የተቆረጠ ድንች ላይ የምንፈልገውን ምስል ከቀረፅን በኋላ እላዩ ላይ የህትመት ቀለም በመቀባት በተለያዩ ወረቀቶች ላይ ቀለማቸውን በመቀያየር እናትማቸዋለን። በመድረክ ትወናዎች ላይ የተለያዩ አልባሳቶችንና ቁሳቁሶችን እንዴት መጠቀም እንዳለብንም በዚሁ ክፍለ-ትምህርት ውስጥ የምናገኝ ይሆናል። ተማሪዎች ከዚህ የትምህርት ክፍል በቂ እውቀት እንድታገኙ እና ችሎታችሁን እንድታዳብሩ ያግዛችኋል።

### በዚህ ክፍለ-ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ እና አቻ የእረፍት ምልክቶቻቸውን በመሰየም ያነባሉ።
- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ እና አቻ የእረፍት ምልክቶቻቸው ውስጥ ያሉ ቀላል ምቶችን ሰምተው ይጽፋሉ።
- ሙሉ ኖታ፣ግማሽ ኖታና ሩብ ኖታዎችን በመጠቀም ዶ፣ሬ፣ሚ (Do, Re, Mi) ድምፆችን ይዘምራሉ።
- የባለ ቀለም ወረቀት (ሞዛይክ) ስራን ይለምዳሉ
- ከህትመት ስራ ጋር ይተዋወቃሉ
- በቴአትር ትወና ጥበብ ውስጥ የምንገለገልባቸውን ቁሳቁሶች ያውቃሉ።

## 2.1. የሙዚቃ ኖታዎችን መሰየም ብሎም መጻፍ

### መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ትምህርታችሁ ላይ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶቻቸውን መሰየም ተምራችኋል። በዚህ ምእራፍ ደግሞ አጻጻፋቸውን እና አጨዋወታቸውን ትማራላችሁ።

### ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ተማሪዎች ስልተ ምቶችን እስከ ሩብ ኖታና እረፍት ያነባሉ።
- ተማሪዎች ዶ ሬ ሚ ልምምዶችን ያደርጋሉ።

**የመወያያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የምታውቁትን አንድ መዝሙር ከጭብጨባ ጋር ዘምሩ።

ለዚህ ክፍል የሚቀርቡት ሙሉ ፣ ግማሽ እና ሩብ ኖታዎች ሲሆኑ የእነዚህ ቅርጽና አጨዋወት በሰንጠረዥ 2.1 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 2.1: የኖታዎች እና አቻ የእረፍት ምልክቶቻቸው አይነትና ዋጋ (አጨዋወት)


| የጨዋታ ምልክት ኖታዎች | አጨዋወቱ | የእረፍት ምልክት ኖታዎች | አጨዋወቱ |
|---|---|---|---|
| 𝅝 | አራት ምት በአንድ ትንፋሽ ሳይቋረጥ መጫወት | 𝄻 | አራት ምት ዝም ማለት/ሳይጫወቱ ማለፍ |
| 𝅗𝅥 = 𝅗𝅥 | ሁለት ምት በአንድ ትንፋሽ ሳይቋረጥ መጫወት | 𝄼 | ሁለት ምት ዝም ማለት/ሳይጫወቱ ማለፍ |
| ♩ = ♩ | አንድ ምት በአንድ ትንፋሽ ሳይቋረጥ መጫወት | 𝄽 | አንድ ምት ዝም ማለት/ ሳይጫወቱ ማለፍ |

ሩብ ኖታ የአንድ ምት የቆይታ ጊዜ ሲኖረው አጨዋወቱም እንደሚከተለው ይቀርባል፡ የግራ እጅን በሆድ አካባቢ አቅጣጫ በመጠኑ መዘርጋትና የግራ እጅ መዳፍን ወደ ላይ በመገልበጥ የቀኝ እጅ የግራውን እጅ መዳፍ መትቶ እንዲመለስ ሲደረግ የሚኖረው የጊዜ ቆይታ የሩብ ኖታን ጊዜ ያህል ነው፡፡ የሩብ ኖታን አነባበብ ለመግለጽ የሚያገለግሉ የሚከተሉትን ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ በተግባር ማሳየትና ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

1. **መነሻ ነጥብ** /የቀኝ እጅ የግራ እጅን መዳፍ ለመምታት የተነሳበት ቦታና ጊዜ)
2. **መካከለኛ ነጥብ** /የቀኝ እጅ የግራ እጅን መዳፍ የመታበት አማካይ ቦታ/
3. **መጨረሻ ነጥብ** /የቀኝ እጅ የግራ እጅን መዳፍ መትቶ መነሻ ነጥብ ዘንድ የተመለሰበት ቦታ/

**ምሳሌ 2.1፡-**


“ላ”ን በአንድ ድምፅ በመዘመር ሩብ ኖታን በሚከተለው ዲያግራም መሰረት መተግበር




የሩብ ኖታ የጊዜ ቆይታ

**ምሳሌ 2.2፡-**


"ላ"ን በአንድ ድምፅ በመዘመር ግማሽ ኖታን በሚከተለው ምስል መሰረት መተግበር




የግማሽ ኖታ የጊዜ ቆይታ

**ምሳሌ 2.3፡-**

ላን በአንድ ድምፅ በመዘመር ሙሉ ኖታን በሚከተለው ስእላዊ መግለጫ መሰረት መተግበር




የሙሉ ኖታ ጊዜ ቆይታ


**ምሳሌ 2.4፡-**

የሩብ የግማሽና የሙሉ ኖታ የእረፍት ምልክቶቹ የእያንዳንዳቸው ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩነቱ የእረፍት ምልክቶችን ምንም ድምፅ ሳይሰማ ጊዜውን ጠብቆ መጫወት ብቻ ይሆናል፡፡

## መልመጃ 2.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጀመሪያ በተናጠል ቀጥሎ በቡድን በመሆን ተለማመዱ

1. ሙሉ ኖታ የጨዋታ ምልክት (ሁለት ሙሉ የጨዋታ ኖታዎችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)




2. ሙሉ ኖታ የእረፍት ምልክት (ሁለት ሙሉ የእረፍት ኖታዎችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)



3. ግማሽ ኖታ የጨዋታ ምልክት (ሁለት የግማሽ የጨዋታ ኖታዎችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)




4. ግማሽ ኖታ የእረፍት ምልክት ግማሽ ኖታ የጨዋታ ምልክት (ሁለት የግማሽ የእረፍት ኖታዎችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)



5. ሩብ ኖታ የጨዋታ ምልክት (ሁለት የሩብ ኖታ የጨዋታ ምልክቶችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)




6. ሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት (ሁለት የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክቶችን ጊዜውን በመጠበቅ ተጫወቱ)





ተማሪዎች ቃላትን ከኖታዎቹ ጋር በማቀናጀት እንዴት መገንባትና መጫወት እንደሚቻል በማየት ለመተግበር ሞክሩ፡፡

**ምሳሌ፡-**





ምሳሌ፡-




ምሳሌ፡-





### መልመጃ 2.2

1. ከዚህ በታች በተሰጡት ሣጥን ውስጥ ያሉ የሙዚቃ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶቹን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ አጨዋወታቸውን ተለማመዱ
2. የኖታዎቹን እና የእረፍት ምልክቶቹን ስም በመጻፍ በሣጥኑ ውስጥ ያለው የምት ብዛት ድምር ስንት እንደሆነ በየ ቡድናችሁ ተወያዩበት፡፡ ከተወያያችሁበት በኋላ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍሉ ተማሪዎች ገለጻ አድርጉ፡፡


ሀ)




ለ)




ሐ)



መ)



ሠ)




ረ)



ሰ)




ሸ)



## መልመጃ 2.3

1. በተለያዩ ኖታዎች እና የእረፍት ምልክቶች ከታች በምሳሌ ላይ እንደተቀመጠው አይነት ሶስት የምት አይነቶችን መስርቱ፡፡ የመሰረታችሁትን በቡድን በመሆን ተጫወቱ (አንብቡ)


**ምሳሌ፡-**





## መልመጃ 2.4

1. በመጀመሪያ ያለጭብጨባ በቃላት ብቻ፤ቀጥሎ በጭብጨባ በመጨረሻም በጭብጨባና በቃላት የሚከተሉትን የኖታ ምልክቶች (ምቶች) ተጫወቱ፡፡


ሀ)





ለ)





ሐ)





መ)




ሠ)





ረ)




ሰ)




ሸ)




## መልመጃ 2.5

1. በግል ወይም በቡድን ሙሉ፣ ግማሽና ሩብ ኖታዎችን (የጨዋታና የእረፍት ምልክቶችን) በመቀላቀል አምስት የምት አይነቶችን አዘጋጁ
2. ያዘጋጃችኋቸውን የምት አይነቶች ለክፍሉ ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ አሳዩ

## መልመጃ 2.6

የሚከተሉትን ስልተ-ምቶች በትክክል ጻፉና ተጫወቱ


ሀ) 


ለ) 


## 2.1.1. የድምፅ ልምምድ (ሶልፌጅ)


በሶልፌጅ የድምፅ ልምምድ ትኩረት ከሚሰጥበት አንዱ ክፍል ነው። የድምፅ ልምምዱ (ዶ፤ሬ፤ሚ) ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ መሰረት በማድረግ ይሆናል። የድምፅ ልምምዱ የሚያተኩረው ዶ-ሬ-ሚ ን መሰረት በማድረግ በተዘጋጁ ቀላል ስልተ-ምቶች ላይ ነው፡


በዚህ መሰረት በቀጣይ የተሰጡትን ስልተ-ምቶች ከስር ያሉትን ፊደላት በመጠቀም የጊዜ ቆየታቸው ሳይዛነፍ በመቁጠር በቀላሉ ሶልፌጀን መረዳት ይቻላል፡፡

1.



2.



3.



4.



5.



## 2.2. የባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ እና ከተዘጋጁ ማተሚያዎች ህትመት መስራት

### መግቢያ

በጥበብ ስራ ውስጥ የተለያዩ የቅርፃ ቅርፅ አይነቶችን እንደየ መልካቸው በተገቢው ቦታ ቀለማቸውን በማመሳሰል የተቆራረጡ ባለቀለም ወረቀቶችን በመጠቀምና በመገጣጠም ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ምስሎችን የምንሰራበት ዘዴ ነው፡፡ ሌላው የህትመት ስራ ስንል የተለያዩ የህትመት ዘዴዎችን በመጠቀም ድንች ፣ በጣውላ ወዘተ ላይ ጽሁፎችንና ሥዕሎችን በመቅረጽ ብሎም ቀለምን በመጠቀም የምናትምበት ስነ-ዘዴ ነው፡፡

## በዚህ የትምህርት ርእስ መጨረሻ

- ተማሪዎች ስለ ባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ አሰራር ዘዴ ይረዳሉ።
- ተማሪዎች የባለ ቀለም ወረቀቶችን በመገጣጠም ሥዕሎችን ሰርተው ያሳያሉ።

### የመወያያ ጥያቄ



- ❖ ተማሪዎች ስለ ባለ ቀለም ወረቀት ስራ ከዚህ በፊት የተማራችሁትን ትምህርት መሰረት በማድረግ በቡድን ተወያዩ ።
- ❖ ተማሪዎች ስለህትመት ያላችሁን ግንዛቤ ለመምህራችሁ አስረዱ።

## የባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ

የባለ ቀለም ወረቀት/ሞዛይክ/ ስራ በዕይታ ጥበብ ውስጥ የሚካተት ሲሆን ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች በተለያየ ቅርጽ እየቆራረጥን በሳልነው ሥዕል ላይ የምናጣብቅበት ሂደት ነው። የምንፈልጋቸውን ስዕሎች በምንፈልገው መልክ የቀለም ወረቀቶችን እየቆራረጥን የምንለጥፍበት ሂደት ነው።

## የባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ አሰራር ስነ-ዘዴ

- በመስመር ንድፍ ሰርቶ ማዘጋጀት
- የተለያዮ ቀለም ወረቀቶችን ማዘጋጀት
- በተለያየ ቅርፅ የቀለም ወረቀቶችን መቆራረጥ
- የተቆራረጡ ወረቀቶችን በተሰራው ንድፍ ላይ ትንሽ ክፍተት በመተው እንደ ቀለሙ ስዕሉ ላይ በማጣበቂያ መለጠፍ
- እስከሚደርቅ ድረስ ማጣበቅ እና ማየት

ምስል 2.1: የባለ ቀለም ወረቀት ሞዛይክ ስራ

**መልመጃ 2.7**

1. የባለ ቀለም ወረቀት |ሞዛይክ| አሰራርን በአጭሩ ግለፅ::
2. የባለ ቀለም ወረቀቶችን በሶስት ማዕዘን ቅርፅ በመቆራረጥ በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ ያሉ እቃዎችን ሰርታችሁ አሳዩ
3. በባለ ቀለም ወረቀት የእንስሳቶችን ሥዕል ሰርታችሁ አሳዩ
4. ስማችሁን በባለ ቀለም ወረቀት /ሞዛይክ/ ሰርታችሁ አሳዩ

## 2.2.1. ከተዘጋጀ ማተሚያ ህትመት ዘዴ

ህትመት የምልክት ወይም የሥዕል አይነቶች በአንድ ወይም ብዙ ቀለሞች በመስራት መልዕክቶችን እንዲሁም ሀሳቦችን በቀላሉ መግለጽ የምችልበት ዘዴ ነው:: ተማሪዎች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ምልክቶችን እና ሥዕሎችን በማስተዋል ለትምህርታቸው ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ በቀላሉ መስራት ይችላሉ:: ህትመት (የድንች ህትመት) ማለት የባህላዊ ህትመት ዓይነት ሲሆን በቀላሉ በአካባቢያችን ከምናገኛቸው ቁሳቁሶች የምንሰራቸው ናቸው:: የድንች ህትመት ለመስራት አንድ ድንች ለሁለት ተቆርጦ የምንፈልገውን ቅርጽ፣ ሥዕል፣ ምልክት እንድሁም ጽሁፎችን በድንቹ ላይ በመቅረጽ ከዚያም በተሰራው ቅርጽ ላይ ቀለም በመቀባት በተለያዩ ወረቀት እና ጨርቆች ላይ ደጋግሞ በማተም የምንፈልገውን ህትመት በቀላሉ ማተም እንችላለን::

### ሀ. የድንች ህትመት አሰራር ቅደም ተከተል

- ድንቹን ለሁለት መቁረጥ
- በተቆረጠው ድንች ላይ ሥዕል (ቅርጽ) መስራት.
- ድንች ላይ የተሰራውን ሥዕል ቆርጦ በማውጣት ቀለም መቀባት
- የተቀባውን ሥዕል ወረቀት ላይ በማስደገፍ ማተም::

**የህመት ዘዴ ቅደም ተከተሎችን ከሚከተሉት ምስሎች ላይ ተመልከቱ**





ምስል 2.2: የድንች ላይ ላይ ሥዕል



ምስል 2.3: የምንፈልገውን የቀለም አይነት ቅርፁ ላይ ሲቀባ



ምስል 2.4: ቀለም የተቀባውን ቅርጽ ንፁህ ወረቀት ላይ ሲታተም

በድንች የህትመት ዘዴ ሁለት ቀለማትን ማተም የሚቻል ሲሆን ሂደቱም አንድ ድንች ሁለት ቦታ ተቆርጦ ሁለቱም ላይ ተመሳሳይ ሥዕል በመቅረጽ እና የተለያየ ቀለም በመቀባት ማተም ነው።



ምስል 2.5: የድንች ህትመትን በተለያዩ ቀለማት ማተም


## ለ. የእንጨት ህትመት ( ውድ ከት)

የእንጨት ህትመት የምንለው የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች በኪነ-ንድፍ አጥንተው በሚያዘጋጁት ሀሳብ ዙርያ ለህትመት እንደሚመች ተደርጎ የማተሚያውን ቁስ በተለያየ መቁረጫ እና ማስተካከያ በመስራት ቀለም እንዲነካው የምንፈልገውን ቦታ ከፍ ብሎ እንዲቀር በማድረግ የምናትምበት ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ አንድ ጥሩ የሆነ የህትመት ንድፍ አዘጋጅተን ለህትመት እንዲሆን አድርገን ካዘጋጀን በኋላ ብዙ አይነት ተመሳሳይ የህትመት ውጤቶችን እንድንሰራበት ያስችለናል። ከጣውላ በተዘጋጀ የሚሰራ ህትመት በጥንት ጊዜ የሚታተም ባህላዊ የህትመት አይነት ነው።በልብስ ላይ እና በጨርቅ ላይ ለመጀመርያ ጊዜ ይሰራ እንደነበር እና በአምስተኛው ክፍለዘመን በቻይና ጽፎችንና ሥዕሎችን በወረቀት ላይ በማተም ይጠቀሙ ነበር። በ1400 አካባቢ ጃፓን በእንጨት

ላይ ሥዕሎችን በመስራት እና ወረቀት ላይ በማተም የህትመት ስራ እየተሰራ እንደነበረ ታሪክ ይገልጻል፡፡

## የጣውላ ላይ ህትመት አሰራር፡-

- በወረቀት ላይ ምስሉን በመሳል መለማምድ
- በወረቀት ላይ የተሰራው ምስል በጣውላ ላይ ደግሞ መሳል
- በጣውላ ላይ የተሳለው ሥዕል በጣውላ መቦርቦርያ መሳርያ ወይም በሹል ብረት በመፋቅ መቅረጽ
- የተቀረጸው ምስል ላይ በመዳመጥ ቀለም መቀባት
- በመጨረሻም ወረቀት ወይም ጨርቅ ላይ በማጣበቅ ማተም



ምስል 2.6: በወረቀት ላይ የተሰራ ንድፍ



ምስል 2.7: የተሰራው ምስል በጣውላ ላይ ሲሳል



ምስል 2.8: የተቀረጸው ምስል ላይ በመዳመጥ ሲቀባ



ምስል 2.9: ወረቀት ላይ ወይም ጨርቅ ላይ ይታተማል



ምስል 2.10: የወረቀት ህትመቱ የመጨረሻ ውጤት

**መልመጃ 2.8**

5. በባለ አንድ ቀለም የድንች ህትመት ሰርታችሁ አሳዩ
6. ባለ ሁለት ቀለም ያለው የድንች ህትመት ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ
7. በጣውላ ላይ ህትመት የሚያሳይ ሥዕል ሰርታችሁ አሳዩ



## 2.3. ቴአትርን በመድረክ አልባሳት እና ቁሳቁስ መስራት

### መግቢያ

በቴአትር ትወና ወቅት ከሚያስፈልጉን መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ የመድረክ ቁሳቁስና አልባሳት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። የቴአትር መከወኛ ቁሳቁስ የምንላቸው ተንቀሳቃሽ ወይም በእጃችን ልናንቀሳቅሳቸው የምንችላቸው ናቸው። እነዚህን የትወና ቁሳቁስና አልባሳት የሚያዘጋጀው ባለሞያ የቴአትር ቁሳቁስ አዘጋጅ ብለን ልንጠራው እንችላለን።

## በዚህ የትምህርት ርእስ መጨረሻ

- ተማሪዎች ስለ ቴአትር ቁሳቁሶችና አልባሳት ይረዳሉ
- ተማሪዎች የቴአትር ቁሳቁሶችና አልባሳትን በመጠቀም ቴአትር ሰርተው ያሳያሉ

### የመወያያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ስለ ቴአትር አልባሳትና ቁሳቁስ የምታውቁትን በቡድን ሆናችሁ በመወያየት ለመምህራችሁ ሀሳብ ስጡ

## 2.3.1. የቴአትር ቁሳቁስ አይነቶች

አብዛኛዎቹ የቴአትር ቁሳቁሶች በዕለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ የምንጠቀማቸው ቁሳቁስ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ስንጠቀማቸው ለመድረክ ትወና የሚያስፈልጉንን መርጠን መሆን አለበት፡፡ የቴአትር ቁሳቁስ አይነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል

- የመድረክ ገጽ (ሲነሪ)
- የመብራት (የኤሌክትሪክ) ቁሳቁሶች
- በትወና ወቅት የምንጠቀማቸው ምግብና መጠጦች
- ወንበርና ጠረጴዛዎች
- የአውደ-ውጊያ (የጦር ሜዳ) ቁሳቁስ
- ተሰባሪ ቁሳቁስ
- ከላይ በዝርዝር ከተቀመጡት ውስጥ የተወሰኑትን ለአብነት እናያለን፡፡

### የአውደ-ውጊያ ቁሳቁስ

እነዚህ ቁሳቁሶች ማህበረሰቡ በአውደ-ውጊያ ወቅት የሚጠቀማቸው የቁሳቁስ አይነቶች ሲሆኑ የውጊያ ታሪክን የያዘ የመድረክ ቴአትር ሲኖረን እንዳስፈላጊነቱ ልንጠቀማቸው እንችላለን፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ጠብመንጃ
- ጦር
- ጎራዴ
- ጋሻ

የመሳሰሉትና እናንተም በየአካባቢያችሁ ያሉትን የአውደ-ውጊያ ቁሳቁሶች ያካትታል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች እዚህ ጋር ማወቅ ያለብን አስፈላጊ ነገር በመድረክ ቴአትር ትወና ወቅት ከላይ የተዘረዘሩትን የአውደ-ውጊያ ቁሳቁሶች ተመሳሳያቸውን ከእንጨት በመስራት ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ልንገለገልባቸው ይገባል፡፡

## ሀ. ጋሻ





ምስል 2.11: ጋሻ

## ለ. ተሰባሪ ቁሳቁስ

ተሰባሪ ቁሳቁስ የምንላቸው በባህሪያቸው ሊሰበሩ የሚችሉ የመድረክ ቴአትር የቁሳቁስ አይነቶችን ነው፡፡

**ለምሳሌ 2.1፡-**

- የእንጨት ወንበሮች
- የስኳር/ጨው ማስቀመጫ ጠርሙሶች
- ከመስታወት የተሰሩ ቁሳቁሶች

የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን በቴአትር ትወና ወቅት ቢሰበሩ እንኳን የከፋ ጉዳት እንዳያደርሱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡



ምስል 2.12: ወንበር

## ሐ. የመብራት (የኤሌክትሪክ) ቁሳቁስ

እነዚህ ቁሳቁሶች ለቴአትር ትወና እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ለአብነት ለመጥቀስ ያህል

- የራስጌ መብራት
- መብራቶች የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ::

## 2.3.2. ለቴአትር ትወና የሚያስፈልጉ አልባሳት

አልባሳት በቴአትር ትወና ወቅት የምንገለገልባቸው ልብሶች እና የገጽ ቅብ ግብዓቶች የመሳሰሉት ሲሆኑ የአንድን ግለሰብም ሆነ ቡድን ጾታ፣ አካባቢ፣ ባህል፣ ሞያ፣ ዜግነት የመሳሰሉትን ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው:: አልባሳት የሚለውን ቃል በጥሬው ብናየው ልብሶችን ይገልጻል::

ለምሳሌ 2.2:-

- የስራ አልባሳት
- የውዝዋዜ አልባሳት
- የዘወትር አልባሳት

ነገር ግን በቴአትር ትወና ወቅት አልባሳት ብዙ ጉዳዮችን አካቶ ሊይዝ ይችላል::



ምስል 2.13: የተለያዩ አልባሳት

### የአልባሳት አይነቶች

የአልባሳት አይነቶች ብዙ ቢሆኑም ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን ይመስላሉ

- ሀገራዊ (አካባቢያዊ) አልባሳት
- የመድረክ ትወና አልባት

### ሀገራዊ (አካባቢያዊ) አልባሳት

እነዚህን አልባሳት በምንጠቀምበት ወቅት ሃገርን ወይም አካባቢን ይገልጻሉ:: በሃገራችን (አካባቢያችን) ያሉ የተለያዩ እሴቶቻችንን በልዩነት እና በሙላት መሳየት የሚችሉ ናቸው::

**ለምሳሌ:-**

ድንጉዛን ለብሰን ስንታይ የጋሞ ማህበረሰብን በሚገባ እናስታውሳለን::



ምስል 2.14: የጋሞ አካባቢ አልባሳት

## የመድረክ ትወና አልባሳት

እነዚህ የአልባሳት አይነቶች በመድረክ ትወና (ቴአትር) በምናሳይበት ወቅት እና ህዝብ በሚሰበሰብባቸው በዓላት (ማህበራዊ ክንውኖች) ላይ የምንለብሳቸው ናቸው፡፡ በትወና ወቅት እነዚህን አልባሳት ስንጠቀም ብዙ መልእክቶችን እንዲያስተላልፉ አድርገን መሆን አለበት፡፡

**ለምሳሌ 2.3፡-**

- የአየር ንብረትን
- አካባቢን
- ሁኔታን ወዘተ.

## አልባሳትን ማዘጋጀት

አልባሳትን በምናዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን ሂደቶች ታሳቢ ማድረግ አለብን፡፡

- ማዘጋጀት
- መቁረጥ
- ማስተካከል
- ፓተርን ጠብቆ መስፋት
- ዲዛይን ማድረግ

**መልመጃ 2.9**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመስክ ዳሰሳ ለዩና በክፍል ውስጥ ተወያዩ
2. እናንተ የምትኖሩበት ማህበረሰብ አለባበስ ምን ይመስላል?
3. በአካባቢያችሁ ከወዳደቁ ጨርቆች መርፌና ክር በመጠቀም ለአሻንጉሊት የሚሆኑ አልባሳትን ሰፍታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ
4. በቡድን ሆናችሁ የቴአርት ቃለ-ተውኔት በመጻፍና በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን ቁሳቁስና አልባሳትን በመጠቀም አጭር ድራማ ስሩ

# ማጠቃለያ

በዚህ ክፍለ-ትምህርት የጊዜ ምልክቶች የሚባሉት ጊዜውን የሚያሳዩንን ኖታዎችን (የጨዋታ/የድምጽ) እና የእረፍት ምልክቶቻቸውን አይተናል፡፡ የጊዜ ምልክቶች የምንላቸው የጨዋታ (የድምጽ) እንዲሁም የዝምታ (የእረፍት) በመባል በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ የኖታ ምልክቶችና የእረፍት ምልክቶች የየራሳቸው ዋጋና የአቆጣጠር ስልት ያላቸው ሲሆኑ ሂሳባዊ ባህሪም አላቸው፡፡ ተማሪዎች በዚህ ክፍለ-ትምህርት የኖታና የእረፍት ምልክቶችን አውቃችኋል፡፡ በተለይ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶችን ሂሳባዊ ባህሪም እንድትረዱ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ እንደዚሁም በተለያየ መንገድ ዋጋቸውን ቆጥራችኋል፡፡ ሌላው በዚህ ክፍለ-ትምህርት የተማራችሁት ጽንሰ-ሀሳብ የሶልፌጅ (ዶ ሬ ሚ...) የመዘመርን ክህሎት ነው፡፡ ጆሮን በማሰልጠን በጥሩ ድምጽ በመዘመር የዝማሬ ክህሎታችሁን እናዳብራችሁበት ይታመናል፡፡

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪም በእይታ ጥበብ ውስጥ የባለ ቀለም ወረቀት (ሞዛይክ) ስራን ጽንሰ-ሀሳብ ተረድታችኋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተጨማሪም የህትመት ስራ (ምሳሌ፡- የድንች ህትመት) በንድፈ-ሀሳብም ሆነ በተግባር እንድትለማመዱ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትም በስፋት ተካተው የሚገኙ እንደ መሆኑ መጠን በቂ እውቀት እንዳገኛችሁ መገመት አያዳግትም፡፡

በመድረክ ትወና (ቴአትር) ጥበብም ላይ ሰፊ ግንዛቤ ለመፍጠር ተሞክሯል፡፡ በተለይ የቴአትር ግብአቶችን በአይነታቸው በመክፈል የሚሰጡትን አገልግሎትም ጭምር በስፋት ለማየት ሞክረናል፡፡

# የማጠቃለያ መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ የቴአትር ቃለ-ተውኔት በመጻፍና በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን ቁሳቁስና አልባሳትን በመጠቀም አጭር ድራማ ስሩ፡፡
2. ባለ ሁለት ቀለም ያለው የድንች ህትመት ሥዕል አትሙ፡፡
3. የባለ ቀለም ወረቀቶችን በሶስት ማዕዘን ቅርፅ በመቆራረጥ በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ ያሉ እቃዎችን ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
4. በመጀመሪያ ያለጭብጨባ በቃላት ብቻ፣ ቀጥሎ በጭብጨባ በመጨረሻም በጭብጨባና በቃላት የሚከተሉትን የኖታ ምልክቶች (ምቶች) ተጫወቱ፡፡

ሀ)



እ - ን - ማር በር - ት - ተን

ለ)



ኢ - ት - ዮ - ጵ - ያ ሀ - ገ - ሬ

ሐ)



ወ - ዲያ ወ - ዲህ ዥ - ው ዥ - ው

መ)



ል - ማ - ትን እ - ና - ፍጥን

ሠ)



ደ - ኖ - ችን እ - ና - ልማ

ረ)



ዱብ ዱብ ዱብ ዱብ

ሰ)



ቤ - ተ - ሰ - ቤን አ - ከብ - ራ - ለሁ

ሸ)



ተ ነ ሱ ለ ስ ራ

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የእይታ እና የትወና ጥበብ ጭብጦች

### መግቢያ

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገርና የብዙ አመታት የታሪክ ባለጸጋ ነች፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ባህል እና እሴቶች ያሏት ሀገር ናት፡፡ ከእነዚህም አንደኛው የባህል (የሃገረ-ሰብ) ሙዚቃዎቿ ናቸው፡፡ ባህል የአንድ ማህበረሰብ ማንነት የሚገለጽበት ወይም የሚታወቅበት ነው፡፡ ይኸውም የአለባበሱ፣ የአመጋገቡ፣ የአጨፋፈሩ ፣ የባህላዊ ዘፈኑ ወዘተ፣ የሕዝቡን ባህላዊ ሕይወት የሚያሳዩ ነፀብራቆች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍለ-ትምህርት ተማሪዎች ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዜማዎችን በመጫወት ትኩረት በመስጠት በትንተና ገለፃ ታደርጋላችሁ፡፡ በመቀጠልም በመወያየት አስተያየታችሁን ትሰጣላችሁ፡፡

በዚህ ክፍለ-ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው የየአካባቢያችሁን ባህላዊ ሙዚቃዎች ከእንቅስቃሴዎቻቸው ጋር በማቀናጀት ለመተንተን እንድትችሉ ሲሆን በመቀጠልም እራሳችሁን ችላችሁ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃዎችን ከእንቅስቃሴ ጋር በማዋሐድ እንድትጫወቱ ለማድረግ ነው፡፡

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ከሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችን ፣ ከሠርግ ሥነ-ሥርዓት ፣ ከአርበኛነት ፣ የአካባቢን ውበት ከሚያንፀባርቁ ወዘተ ድርጊቶች ጋር የተያያዙ የመስክ ጉብኝት ማድረግንና ልምድ ካላቸው ሰዎች በመማርም ሆነ ከመምህራችሁ እና ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት ብዙ ማወቅ ይጠበቅባችኋል፡፡ ይህንን የባህል እሴት ለማስፋፋት የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርት ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በዚህ ክፍለ-ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥ በስፋት የምንዳስሰው የእይታ ጥበብን ከታሪካዊ ዳራው አንጻር መቃኘት ነው፡፡ በተለይም ተማሪዎች የዋሻና የቀለም ቅብ ስራዎችን ጽንሰ-ሃሳብ እንድትረዱ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡ ዋሻ ማለት አንድን ድንጋይ በመፈልፈል እንዲሁም መሬትን በመቦርቦር የምንሰራውና በውስጡም ባሉ ግርግዳዎች

ላይ የተለያዩ የእንስሳትም ሆነ የሰዎችን ምስል የምንቀርጽበት ወይም ተቀርጾ የምናገኝበት ስፍራ ነው፡፡ የቀለም ቅብ ደግሞ ቀለምን በመጠቀም የተለያዩ ሃሳቦችን የምንሰራበት የስነ-ጥበብ አይነት ነው፡፡

ከላይ በተገለጸው መሰረት በዚህ ክፍለ-ትምህርት በዋናነት በተማሪዎች የመኖርያ አካባቢ የሚገኙ የሃገረ-ሰብ ትውን ጥበባት ውጤቶች እና የእይታ ጥበባት አይነት በታሪክ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ መረዳት ብሎም ውዝዋዜዎችን (ጭፈራዎች) መሰብሰብን እና መጫወትን ማወቅ ሲሆን ትምህርቱን ለመተግበር በርካታ ተማሪ ተኮር ክንዋኔዎች ትኩረት ተሰቶባቸዋል፡፡ ተማሪዎች የሃገረሰብ ታሪኮችን በመሰብሰብ ፣ በማጥናትና በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ በመንገር ለባህላችሁ ያላችሁን እውቀት አሳድጉ፡፡

**በዚህ ክፍለ-ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁት አነስተኛ የመማር የብቃት አሃዶች የሚከተሉት ናቸው ፡፡**

- የሃገረ-ሰብ ዜማዎችንና ውዝዋዜዎችን ይለያሉ
- የሃገረሰብ ትውን ጥበባትን በመዝሙር፣ በውዝዋዜ ፣ በመድረክ ትወና እንዲሁም በድምጽ አልባ ትወና ያቀርባሉ
- የሃገረ-ሰብ ዜማዎችን እና ውዝዋዜዎችን በዘውጋቸው ይከፍላሉ
- የእይታ ጥበብ ታሪክን (የዋሻ ጥበብ ፣ የቀለም ቅብ ጥበብ) የመሳሰሉትን ይለያሉ
- ጉብኝት አድርገው ግብረ መልስ ይሰጣሉ

## 3.1. ሃገረሰባዊ ዜማዎችና የውዝዋዜ (የዳንኪራ) አይነቶች

### መግቢያ

በኢትዮጵያ በእያንዳንዱ ክልል በርካታ ባሕላዊ ዜማዎች ይገኛሉ፡፡ ባሕላዊ ዜማዎቹ ከሥራ፣ ከእርሻና ከእንስሳት ማርባት፣ ከሕብረት፣ ከመልካም ሥነ ምግባር፣ ከበዓላት ሥነ ሥርዓቶች /ድርጊቶች/ ወዘተ… ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ባህላዊ ዜማ የራሱ የሆነ አተገባበር እና የጨዋታ ስርአት አለው፡፡ ባህላዊ (የሃገረሰብ) ዜማዎቹ በሙዚቃ መሳሪያዎች ሊታጀቡ ይችላሉ፡፡ የራሳቸውም አልባሳት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በግጥም ከሚቀርቡትና ከሚዜሙት የስነ-ቃል አይነቶች አንደኛው ወገን ባህላዊ ዘፈኖችን ያጠቃልላል፡፡ ባህላዊ (የሃገረሰብ) ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚዘፈኑ የማሕበረሰቡን ልዩ ልዩ መልኮች ሊያሳዩ የሚችሉ አስደሳች የስሜት መግለጫዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ማሕበረሰብ እንደየ ባህሉና እንደ አኗኗር ስልቱ ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች አሉት፡፡

**ለምሳሌ፡-**

የሥራ ዘፈን ፣ የክብረ በዓል ዘፈን፣ የሰርግ ዘፈን ፣ የፍቅር ዘፈን ፣ የአምልኮ ሥርዓት ዘፈን ፣ የልጆች ጨዋታ ዘፈን፣ የእሹሩሩ (ህጻን ልጅ ማባበያ) ወዘተ እየተባሉ ይመደባሉ፡፡ ለአብነት ያክል የሥራ ዘፈንን ብንወስድ ከሚሰራው ሥራ ጋር ግንኙነት በማድረግ በቡድን (በደቦ) እየተሠራ በሚዘፈነው ላይ ይበልጥ ይታያል፡፡ በዚህ ይዘት ላይ ባህልን ከባህል ለማወዳር ወይም ለማበላለጥ ሳይሆን የምትሰሟቸውን ባህላዊ ዜማዎችና ውዝዋዜዎች አድናቆትን እንድትሰጡ ለማድረግ ነው፡፡

## ከዚህ ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- የሃገረ-ሰብ ዜማዎችንና ውዝዋዜዎችን ይለያሉ፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት የሰማችሁትን አንድ የሃገረሰብ ዜማ ከውዝዋዜው ጋር ተጫወቱ

## ባህላዊ (የሃገረ-ሰብ) ዜማዎች

የሃገረ-ሰብ ዜማዎች ስንል የባህል ዜማዎች ሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ወይም በአፈ-ታሪክ የሚተላለፉትን ማለታችን ነው፡፡ እነዚህ ዜማዎች በማን እንደተፈጠሩ የሚታወቅ ነገር ስለሌለ ባለቤትነታቸው የህዝብ ነው፡፡ የሃገረሰብ ዜማዎችን በአለማችን የተለያዩ ክፍሎች የምናገኛቸው ሲሆን እንደየ አካባቢው የየራሳቸው መገለጫ አላቸው፡፡ በጥቅሉ ግን የሃገረሰብ ወይም የባህል ዜማዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡፡

- በልምድ የሚዜሙ ዜማዎች ናቸው
- በቃል ከቤተሰብ ወይም ከአካባቢ የሚወረሱ ናቸው
- የአንድን ሃገር ወይም አካባቢ ባህልና እሴት ያንጸባርቃሉ
- አንዳንዶቹ ዜማዎች ከበዓላት አከባበር ፣ ከሰርግ ወይም ከለቅሶ ፣ ከጀግንነት፣ ከደቦ ስራ ፣ ከእረኝነት ፣ እንዲሁም ልጅ ከማሳደግ (የእሹሩሩ) ዜማዎች ጋር ይያያዛሉ
- ከሌሎች አካባቢ ዜማዎች ጋር የመወራረስ እድልም አላቸው፡፡

### 3.1.1. የሃገረሰብ ዜማ አይነቶች

የሃገረሰብ ዜማዎች ብዙ አይነት ናቸው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ፡-

- ከአካባቢና ከበዓላት ጋር የሚያያዙ የሃገረሰብ ዜማዎች
- የፍቅር የሃገረሰብ ዜማዎች
- የስራ የሃገረሰብ ዜማዎች
- የጀግንነት የሃገረሰብ ዜማዎች
- የህጻናት የሃገረሰብ ዜማዎች

## 3.1.2. የኢትዮጵያ የሃገረሰብ ሙዚቃ ታሪክ

ኢትዮጵያ በባህላዊ ሙዚቃ ሰፊ ታሪክ ያላት ሃገር ከመሆኗም በላይ በየትኛውም የውጪ ወራሪ ጠላት ተሸንፋ የማታውቅና ቅኝ ያልተገዛች ሃገር ናት። እጅግ በጣም የተለየ የሃገረሰብ የሙዚቃ ባህል ያላት መሆኗም ይታወቃል። የኢትዮጵያ የሃገረሰብ ሙዚቃ በውስጡ የተለያዩ የባህል ሙዚቃዎችንና ማጀቢያ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የያዘ ሲሆን ከአንድ ሺህ አመት በላይ እድሜንም አስቆጥሯል። ኢትዮጵያ ከሰባ አምስት በላይ ብሄረሰቦች በአንድ ላይ ተዋደውና ተከባብረው የሚኖሩባት ሃገር እንደመሆኗ መጠን እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ልዩ የሆነ የሃገረሰብ ዜማ እና ማገለጫዎች አላቸው።

## 3.1.3. የሃገረሰብ (የባህል) የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነትና አጠቃቀም

የሃገረሰብ የሙዚቃ መሳርያዎች በባህሪያቸው እንደሚከተለው ልንከፍላቸው እንችላለን። እነርሱም፦

ሀ. የክር የባህል መሳርያዎች

ሐ. የምት የባህል መሳርያዎች

ለ. የትንፋሽ የባህል መሳርያዎች

### ሀ. የክር የባህል መሳርያዎች

እነዚህ የሀገረሰብ የሙዚቃ መሳርያ አይነቶች በዋናነት ድምጽ የሚፈጥሩበት ሂደት የተወጠሩ ክሮችን በመግረፍ ወይም በመደርደር (ለቀማ) ስነ-ዘዴ ሲሆን በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የተወሰነ የአሰራር ልዩነት ይኖራቸዋል።



ምስል 3.1: ዲታ (የክር መሳርያ)

### ለ. የትንፋሽ የባህል መሳሪያዎች

እነዚህ የሀገረሰብ የሙዚቃ መሳርያ አይነቶች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ በዋናነት ድምጽ የሚፈጥሩበት ሂደት ትንፋሽን ወደ ውስጣቸው በመንፋት ዘዴ ሲሆን በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የተወሰነ የአሰራር ልዩነት አላቸው።



ምስል 3.2: የሃገረሰብ የትንፋሽ መሳርያዎች

## ሐ. የምት የባህል መሳርያዎች

እነዚህ የሀገረሰብ የሙዚቃ መሳርያ አይነቶች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ በዋናነት ድምጽ የሚፈጥሩበት ሂደት በምት ዘዴ ሲሆን በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የተወሰነ የአሰራር ልዩነት አላቸው።



ምስል 3.3: የሃገረሰብ የምት የሙዚቃ መሳርያ

## 3.1.4. ባህላዊ (የሃገረ-ሰብ) ዜማዎችን እና ውዝዋዜዎችን መሰብሰብ

- የአካባቢ ውበትን የሚያንጸባርቅ
- ሥነ ምግባርን የሚያንፀባርቅ
- የእንስሳትን ተፈጥሮ የሚያንፀባርቅ
- የአእዋፋትን ተፈጠሮ የሚያንባፀርቅ

**መልመጃ 3.1**

1. አንድ የባህል ዜማ ከውዝዋዜው ጋር በቡድን በማጥናት በክፍል ውስጥ አቅርቡ
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የባህል ዜማ እና ውዝዋዜ የሚያውቁ ሰዎችን አጭር የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸውን በመጠየቅ አሰባስባችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በክፍል ውስጥ አብራሩ።

# 3.2. የዕይታ ጥበብ አይነቶች በታሪክ ውስጥ (የዋሻ እና የቀለም ቅብ) ጥበብን መለየት

**መግቢያ**

የዋሻ ውስጥ ጥበባትና የቀለም ቅብ ስንል በታሪክ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ ለትውልድ እየተላለፉ የመጡ የጥበብ ስራዎች ናቸው። የዋሻ ውስጥ ጥበባት የጥንት ሰዎች በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ በሆኑ ዋሻዎች ውስጥ የሰው ልጅ የእጅ ጽሁፍ ከመጀመሩ በፊት የተለያዩ ድንጋዮችን በመቦርቦርና ቅርጽ በማውጣት በዋሻው ውስጥ የተለያዩ ቅርጻቅርጾችን የሚሰሩበት ሲሆን የቀለም ቅብም ከጥንት ጀምሮ በዋሻ ውስጥ ስዕሎች ላይ ይቀቡ ነበር። በጥንት ጊዜ ቀለምን በውሃ በመበጥበጥ የተለያዩ ምስሎችን በግድግዳ ላይ ይስሉ እንደነበር ታሪክ ያሳያል።

## ከዚህ ርዕስ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- የእይታ ጥበብ አይነቶችን ከታሪክ አንጻር ይገነዘባሉ።
- የዋሻና የቀለም ቅብ ጥበብን ይረዳሉ።

**የመወያያ ጥያቄ**

- ስለ እይታ ጥበብ ታሪክ ከዚህ በፊት ያላችሁን ግንዛቤ በቡድን ተወያዩ

## 3.2.1. 3.2.1. የዋሻ ውስጥ ጥበብ

የሰው ልጆች በዋሻ ውስጥ እየኖሩ የሰሯቸው የዋሻ ጥበብ በቅድመ ታሪክ በርካታ ሲሆኑ የእጅ ጽሁፍ ስራ ከመጀመሩ በፊት በዋሻ ውስጥ ድንጋዮችን በመቦርቦርና ቅርጽ በመስጠት የተለያዩ የሰውና የእንስሳት እንዲሁም የአደን መሳሪያዎችን እና የመሳሰሉትን በዋሻ በግድግዳ እና በድንጋይ ላይ ይስሉ ነበር።




ምስል 3.4: የዋሻ ሥዕል መስሪያ ቁሳቁስ

በአለም ላይ የተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የዋሻ ጥበብ ስራዎች ተሰርተዋል። ከነዚህም ውስጥ አውሮፓ አፍሪካ አውስትራሊያ አህጉራት የዋሻ ላይ ስዕሎች የሚገኙባቸው አህጉራት ናቸው። አፍሪካ ቀደምት የሆነ የተለያዩ የዋሻ ጥበብ ስራን በዓለት ላይ ተቀርጠውና ተቦርቡረው ተሰርተው ይገኛሉ። ከሶስት ሺህ አመታት በፊት በናሚቢያ በ1969 ኢ.ኤ.አ የተገኘ ዋሻ ላይ የፊት ምስል ያላቸው የዋሻ ውስጥ የጥበብ ስራዎች ተቀርጸው ይገኛሉ።



ምስል 3.5: በናምቢያ በ1969 ኢ.ኤ.አ የተገኘ ዋሻ

በሀገራችንም ካሉ የዋሻ ውስጥ ጥበባት በቅድመ ታሪክ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኘው ከምስት መቶ አመታት በፊት በጥቁር እና ነጭ እንዲሁም በቀይ ቀለም የተሰሩ የእንስሳትና የሰው ምስል ያላቸው የዋሻ ውስጥ ጥበባት ይገኛሉ። በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ከደቡብ ምስራቅ በ 28 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ሲገኝ የዋሻው ሥም ጎዳ አጃዋ በመባል ይታወቃል።



ምስል 3.6: የጎዳ አጃዋ ዋሻ

የዋሻ ሥዕሎች በአብዛኛው ግርግዳ ወይም መሬት ላይ የተሰሩ ናቸው። ምስሎቹ የሚሰሩባቸው ቀለማት በብዛት ቀይ እና ጥቁር ሲሆኑ ቀለሞቹም የሚገኙት ከከሰል ጥቁር ቀለም በማዘጋጀትና ከአፈር ቀይ ቀለም በማዘጋጀት ነው። በዋሻ ግድግዳ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተለጠፈው ዝርግ ቅርጽ የዋሻ ጥበብ መስራት እንደተጀመረ ያመለክተናል። ለስላሳ የሆነ ግድግዳ ላይ በእጅ እና ሹል በሆነ ጠንካራ መፈልፈያ እየተፈለፈለ የሚሰራ የጥበብ አይነት ነው።



ምስል 3.7: የዋሻ የጥበብ ስራ

**መልመጃ 3.2**

1. የዋሻ ጥበብን እና የቀለም ቅብ ልዩነትን በዝርዝር አስረዳ።

## 3.2.2. የሥዕል ስራ (ኪነ-ቅብ) በታሪክ ዓውድ

የዋሻላይ ስዕሎች የተሳሉበት ቀለም በአብዛኛው አንድ ወጥ በሆነ ጥቁር ወይም ቡናማ ቀለም ነው። ጥንታዊ ስዕሎች በዋሻ ላይ ለሚሰሯቸው ስዕሎች ጥቁር ቀለምን ከአፈር በማዘጋጀት እንዲሁም ቀይ ቀለምን የእንሣቶችን ደም እና ቀይ አፈርን በመጠቀም የተሳሉ ስዕሎች ናቸው።

### የቀለም ገበታ

የተለያዩ የቀለም አይነቶችን በአንድ ላይ በማዋሃድ የምንፈልገውን የሥዕል አይነት ለመስራት የሚረዳን መሰረታዊ ግብአት ነው።



ምስል 3.8: ጥንታዊ የቀለም ገበታ

**ቀለም መቀቢያ**

የተለያዩ ቀለማትን ለመደባለቅ፣ ለመጻፍ ብሎም ለመሳል የምንጠቀምበት ግብዓት ነው፡፡



ምስል 3.9: ጥንታዊ ቀለም መቀቢያ

**መልመጃ 3.3**

በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ለስዕል መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን አዘጋጁ

## 3.3. ሃገረሰባዊ ታሪኮችን መንገር

### መግቢያ

በአካባቢያችን የሚኖሩ ሰዎች ባህላዊ ታሪኮችን ያወራሉ ብሎም ይሰማሉ፡፡ ቆየት ያሉ ታሪኮችን መስማት ብዙዎቻችንን ያዝናናናል፡፡ ከማዝናናት በዘለለም እርስ በእርስ እንድንቀራረብ እና የተለየ ልምድ እንድናገኝ ይረዱናል፡፡ አንድ ታሪክ ጠንካራ የሚባለው ካለፈው ታሪኮቻችንና እሴቶቻችን ጋር የተናበበ ሲሆን ነው፡፡ ጥንታዊ ታሪኮች ከትውልድ ወደ ትውልድ በአፈ ታሪክ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው እየተሻገሩ የመጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ታሪኮች እምነቶቻችንን በህይወት ውስጥ ያሉ ተስፋዎቻችንን እና ስጋቶቻችንን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ታሪክ የሚያስተምረን ቁምነገር በውስጡ የያዘ ነው፡፡

**በዚህ ክፍለ-ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁት የብቃት አሃዶች የሚከተሉት ናቸው**

- የአካባቢያቸውን ታሪክ ያውቃሉ
- ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን ድራማዎች ይጫወታሉ

**የመወያያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ስለ አካባቢያችሁ ታሪክ ያላችሁን ግንዛቤ በቡድን ተወያዩ

### 3.3.1. የመስቀል በአል አከባበር በጋሞ (ዮ ማስቃላ)

ከመስከረም መጀመሪያ ጀምሮ ፣ ከኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በዓል ጋር የሚመሳሰል ፣ ዮ ማስቃላ አከባበር እስከ ወር መጨረሻ ድረስ በድምቀት ይከበራል:: ጋሞ በማስቀላ በዓል ላይ የሰብል ምርት ማብቂያ ወቅት ላይ የሚከበር ጥንታዊ በዓል ነው:: ይህም ከኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ጋር በተቀራራቢ ቀናቶች ስለሚከበር የበለጠ ደማቅ በመሆን ይከበራል:: በዋናነት ፣ በዓመቱ ውስጥ ላበረከቷቸው እና ለወደፊቱ መልካም ነገሮች እንዲኖራቸው ለመጸለይ ለአከባቢው የእግዚአብሔር ስም የሆነውን ፈጣሪን (ጦሳን) ለማመስገን በማሰብ ይሰበሰባሉ:: ዮ ማስቀላ በዓል ጋር በመንደሩ ውስጥ እንደ የሴቶች ቀን (ሶፌ ማስቃላ) እና የእርድ ቀን (ሹሁአማግ) የመሳሰሉ የተለያዩ ባህላዊ ልምዶች ይከሰታሉ:: የጋሞን መስቀል እንደ አብነት አነሳን እንጂ ተመሳሳይ ክንዋኔዎች በተለያዩ አካባቢዎች ይከበራሉ:: የዘመን መለወጫ በዓላት በወላይታ፣ በአሪ፣ በጉራጌ፣ በሃድያ፣ በከንባታ እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች እንደየ ባህላቸው በስፋት የሚከበር በዓል ነው::

#### ሀ. የሴቶች ቀን

የሴቶች ቀን በዶርዜ ማህበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ ባህላዊ ልምምድ ነው:: ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማርች 8 ን አንድ ቀን ብቻ እንደ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሲወስን፤ የዶርዜ ማህበረሰብ በዓመት ውስጥ አስራ ሰባት ቀናት ይሰጣል:: በዓመት ውስጥ በየወሩ የዶርዜ ሴቶች በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር መሠረት ሁል ጊዜ በየወሩ 21 ኛው ቀን የነፃነት ቀን አላቸው:: በተጨማሪም በመስከረም ወር ዮ-ማስቀላ በዓል ሲከበር ሴቶች አምስት ተከታታይ የነፃነት ቀናትን ያገኛሉ:: በእነዚህ ሁሉ ቀናት ሴቶች ከማንኛውም የቤት ውስጥ ሥራዎች ነፃ በመሆናቸው እነዚያን ቀናት ከጓደኞቻቸው ጋር በመዝናናት እና በመጫወት ያሳልፋሉ::

#### ለ. የጋብቻ ስርዓት

በዶርዜ ማህበረሰብ ውስጥ ለማግባት ሦስት የተለያዩ ባህላዊ መንገዶች አሉ:: እነርሱም ማኮ፣ ዳፋ (ጠለፋ) እና ሶሮ ናቸው:: በማኮ ባህላዊ ጋብቻ ውስጥ ፣ ሙሽራዋ ሳታውቀው ወይም ሳትፈቅደው ለምትወደው ሰው የአባቷን ቤት ትታ ወደ እጮኛው ቤት ትሄዳለች:: ይህን ተከትሎ አንድ አማላጅ ወይም ላዛንታሳ በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል ሰላም ይፈጥራል:: በዳፋ ጋብቻ ውስጥ ሙሽራው ወይም አባቱ ልጃገረዷን በመንገድ ላይ ወይም ከገቢያ ሊጠልፉ ይችላሉ:: ሶሬ ጋብቻ በሴት ልጅ እና በቤተሰቧ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ይህ ጋብቻ በጣም ተገቢው እና ትክክለኛውን ባህላዊ ክንዋኔ ተከትሎ የሚደረግ ጋብቻ ነው::

ሁሉም አዲስ የተጋቡ ሴቶች ለሶፌ ማስቃላ ዝግጅት በፈረስ ወደ ገበያ ቅጥር ይመጣሉ:: በዚህ ቦታ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጎደኞቻቸው እና ለዘመዶቻቸው ይታያሉ:: ሴቶች ውበታቸውን የሚያጎላ ነገር በመልበስ እና በመዋብ በዚህ ቦታ ላይ ይቀርባሉ ማለት ነው::የመስቀል በዓል ከመድረሱ በፊት የሚደረገው ዝግጅት ማታቶኮማማ ይባላል:: ይህ ጊዜ በመንደሩ ነዋሪዎች ዘንድ እንደ ቤተሰብ በዓል ይቆጠራል:: በዚህ ምክንያት ሁሉም የቤተሰብ አባላት በቡድን ሆነው አንድ የተመረጠ ሽማግሌ ቤት ይሰበሰባሉ:: ሁሉም የተሰበሰቡ አባላት ይህንን በዓል በተለያዩ የቤተሰብ ጉዳዮች በመደሰት እና በመጫወት ይህንን በዓል ያከብራሉ:: ሁሉም የቤተሰብ አባላት ለሽማግሌ ቤተሰቦቻቸው የለምለም ሳር ስጦታ እና ነጭ አበባዎችን ይዘው ይመጣሉ:: ይህ ስጦታ ፍቅርን፣ መከባበርን እና የረጅም ዕድሜ ምኞትን ያመለክታል:: በዚህ ስጦታ አማካኝነት ሽማግሌዎች ምርቃትና መልካም ምኞት ለቤተሰቦች ይሰጣሉ::

የወጋ ማስቃላ በዓል ከመስከረም 14-17 ድረስ በዶርዜ ማህበረሰብ በድምቀት ይከበራል:: በእነዚህ ቀናት የእርድ ቀን (ሹሁአማማ) በበዓሉ አቅራቢያ ያለውን የገበያ ቀን በመምረጥ በተከበሩ የመንደር ሽማግሌዎች ምርቃት ይካሄዳል:: በዚህ ምክንያት ዋናው የበዓል ቀን ከዓመት ዓመት ይለያያል:: በተወሰነው ቀን መሰረት በዓሉ በአከባቢው ሽማግሌዎች ለጦሳ (ለእግዚአብሔር) ምስጋና በማቅረብ በይፋ መጀመሩ ይበሰራል:: የአካባቢው ማህበረሰብ መስቀልን ዩ ዮ ዮ በማለት አስደሳች የሆነውን የመስቀል ክብረ በዓል ማክበር ይጀምራሉ:: ዋናው በዓል ከመጀመሩ አንድ ቀን በፊት ሰዎች በቤተሰብ ተሰብስበው ምግብ ይመገባሉ:: ይህም ባህላዊ ክንዋኔ ኬሶካት ይባላል:: በመስቀል በዓል አከባበር እለት በተቻለ መጠን ሁሉም የቤተሰብ አባላት በዚህ ዝግጅት ላይ እንዲገኙ ይደረጋል:: በዚህ ቀን ባህላዊ አከባበር የሚከናወነው በተለምዶ ቦዶ በሚባል የገበያ ቦታ ላይ ነው:: በዶርዜ ማህበረሰብ የሚገኙ 12 ቀበሌዎች በአንድ ቦታ ላይ በመሰባሰብ የጭፈራ፣ የምግብ እና ሌሎች ክንዋኔዎችን ያደርጋሉ:: በዚህ ቦታ ከ 700 እስከ 1000 ሰንጋ በሬዎችን በማምጣት የእርድ ስነ-ስርዓት ይፈጸማል:: ይህ ድባብ የመስቀልን በዓል ልዩ እና ማራኪ ያደርገዋል:: ከታረዱ በኋላ ሰዎች በቡድን ተቀምጠው በባህላቸው መሰረት ባህላዊ መጠጦችን በማዘጋጀት በዓሉ ውብ እና ማራኪ እንዲሆን ያደርጋሉ::

መስቀል በጋራ በዓል ከማክበር በተጨማሪ የተጣሉ እና የተጠፋፉ ሰዎችንም ለማገናኘት እና ለማስታረቅ ትልቅ ድርሻ አለው:: የተጣሉ ሰዎች ሲገናኙ ዮ ዮ ዮ ዩ ብለው በመዝለል እና በመተቃቀፍ እርቅ ይፈፀማል ማለት ነው:: ከዛም በረዥም ሳቅ እርስ በርሳቸው ተቃቅፈው በጋራ በዓል በማክበር ያሳልፋሉ:: ሌላው የበዓሉ ድምቀት የሚሆነው እና በቀለማት ያሸበረቀው ክስተት ደመራ (xomppe) በመባል የሚታወቀው ነው:: በዶርዜ መንደር ውስጥ የ xomppe የሚካበረው በሃገራችን ከሚከበረው የደመራ ቀን ጋር ተመሳሳይ ቀን ነው::

## ሐ. ዱቡሻ

ዱቡሻ በመባል የሚታወቁት ባህላዊ አደባባዮች የመንደሩ ልዩ የባህል እና አገር በቀል እውቀት አንዱ ነው። ዱቡሻዎች ለጋሞ የተለያዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ገጽታዎቻቸውን ለመሰብሰብ እና ለማካፈል የሚገለገሉባቸው ትልቅ ቦታዎች ናቸው። ዱቡሻ በዋናነት የአንድ መንደር ነዋሪዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ለሀገር ሽማግሌዎች እንደ ሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ሆኖ ያገለግላል። እንዲሁም ለቅሶ ስርዓቶች ፣ ለማህበራዊ ጉዳዮች ፣ እና ክብረ በዓላት በዓላት የሚከበሩበት ቦታ ነው።



ምስል 3.10: ዱቡሻ ላይ ተሰብስበው የሚያሳይ ፎቶ

በጋሞ ማህበረሰብ ውስጥ ላካ ዱቡሻ የተለይ ልዩ እና በጣም የተከበረ ቦታ ነው፡ ፡ በዓመቱ ውስጥ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን እና ልይ ልዩ ጉዳዮችን ያስተናግዳል። እንዲሁም በዓመት አንድ ጊዜ የመስቀል ክብረ በዓልን ለማክበር ሁሉም ሰው በዚህ ቦታ በጋራ ይሰበሰብበታል። ይህ ቀን በአከባቢው ማህበረሰብ ላካ ቃማ ወይም የላካ ቀን ተብሎ ይጠራል። በዚህ ቀን አስራ ሁለቱ ቀበሌዎች ተሰብስበው መስቀልን በልዩ ልዩ ባህላዊ ክንዋኔዎች ያሳልፉበታል። የዱቡሻ ቦታ ለመንደሩ ነዋሪዎች አንድነትን፣ ደስታን፣ ሰላምን እና ደህንነትን ለረዥም ጊዜ እንዲጠብቁ ለማድረግ ትልቅ ትርጉም አለው። በተጨማሪም በዚህ ቦታ የሚከናወነው ባህላዊ እንቅስቃሴ የመንደሩን ነዋሪዎች የቆዩ ባህሎችን፣ ደንቦችን እና ወጎችን ለቀጣይ ትውልድ በዘላቂነት የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው። ይህ ባህላዊ አደባባይ (ቦታ) በጋሞ ሰዎች ዘንድ ትልቅ ትርጉም ያለው ቦታ ነው።

ዱፌ ማስቃላ መስከረም 28 በዶርዜ መንደር ይከበራል። የልምምድ ፌስቲቫሉ የምረቃ እና የመዝጊያ ሥነ -ሥርዓት በአከባቢው ሽማግሌዎች ይፋ ይደረጋል። ለአንድ ዓመት ሙሉ ለማህበረሰቡ አንድነት፣ ጥንካሬ፣ ጤና፣ ፍቅር እና ሰላም እንዲሆን ይመኛሉ።

ከመስቀል በዓል ጋር ተያይዞ የተለያዩ ማራኪ የባህል ዝግጅቶች ከመስከረም 10 እስከ ጥቅምት 10 ድረስ በመንደሩ ውስጥ ይከናወናሉ፡፡ ይህ ፌስቲቫል የቱሪስት መስህብ ከመሆኑ በተጨማሪ ለአከባቢው ማህበረሰብ ሌሎች በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር በርካታ ሰዎች ወደ አካባቢው በሚመጡበት ጊዜ እንደገቢ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ለአካባቢው ነዋሪዎች ትልቅ እሴት ነው፡፡ ከማህበራዊ-ፖለቲካዊ እይታ አንፃር ፣ የመንደሩ ነዋሪዎችን መስተጋብር እና አንድነት ከቤተሰብ ደረጃ እስከ መላው ማህበረሰብ ለማቆየት ሁሉን አቀፍ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለዚህ ፣ እነዚያ የማይቆጠሩ የማሲ.ቃቅላ እሴቶች ፌስቲቫሉ በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ባሉ ሰዎች ዘንድ መታወቅ እና መጎብኘት አለበት በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም፡፡

## 3.3.2. ከዕንሰት ምግብን የማዘጋጀት ሂደት

ትዮጵያ ለተለያዩ ሰብሎች መነሻ ከሆኑ አገራት ማዕከላት አንዷ ናት፡፡ ዕንሰት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች ከሚገኙት ተወዳጅ የእፅዋት ዝርያዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ እንጨት አልባ ተክል ከሙዝ ተክል ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ረጅምና ወፍራም ነው፡፡ እንደ ሙዝ ፍሬዎችን የማይሰጥ ሥሩ ለምግብነት የሚውል ሰብል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት “ሐሰተኛ ሙዝ” ይባላል፡፡

የእንሰት ተክል በብዙ የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች እንደየባህሉ ሁኔታ ለምግብነት ይውላል፡፡ በዚህም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደ ጣፋጭ ምግብ ይቆጠራል፡፡ በብዙ አካባቢዎች ሰዎች በትልልቅ የእርሻ መሬት ወይም በአነስተኛ የአትክልት ቦታቸው ላይ በማረስ እና በማልማት ለምግብነት ያውሉታል፡፡



ምስል 3.11፡ የዕንሰት ምግብን የማዘጋጀት ሂደት

ዕንሰት እንደ ቆጮ (እንዲሁም Uncca ተብሎ የሚጠራው ጠፍጣፋ ዳቦ) እና ኢቲማ (ገንፎ) ያሉ የተለያዩ ምግቦችን ይዘጋጁበታል። የእንሰት ተክል ለምግብነት ለመዋል አራት ወይም አምስት ዓመት ይወስዳል። ለምግብነት የሚያገለግለው የእንሰት ክፍል ለተወሰነ ጊዜ መሬት ውስጥ በመቅበር ለምግብነት ይውላል። በመጨረሻም ሰዎች እንደየባህላቸው ቆቾ ፣ በኡትታ (ዳቦ) ፣ ሽንዬራ (ገንፎ) እና ኢንሴላ መልክ ይበላል። ሌላው ከዚህ ተክል ክፍል የቡላ እና ደሹቻ ምርቶችን ይሰሩበታል።

ደስሹቻ የእንሰት ትኩስ ክፍል ሲሆን በተለምዶ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦችን ለማዘጋጀት ያገለግላል። አዘገጃጀቱም ልክ እንደ ድንች ከበሰለ በኋላ ሊበላ ይችላል። የእንሰት ዛፍ ከምግብነት በተጨማሪ ቅጠሎቹ ሌላ ምግብ ለማብሰል (ለምሳሌ ዳቦ ለመድፋት) ፣ ገመዶችን እና የቤት ቁሳቁሶችን ለመሥራት ያገለግላል።

**መልመጃ 3.3**

1. የዱቡሻን ታሪክ በጥልቀት በማጥናትና ሂደቱን ከአባቶቻችሁ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።
2. ስላቀረባችሁት የዱቡሻ ታሪክ በቡድን ተወያይታችሁ አስፈላጊነቱ ምን እንደሆነ ለይታችሁ አውጡ።
3. በየአካባቢያችሁ ያሉ ታሪኮችን በድራማ አቅርቧቸው

## ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች መኖሪያ እና የብዙ አመታት የታሪክ ባለጸጋ አገር ነች። በዚህም የተነሳ በርካታ ውብ ባህሎች እና እሴቶች አሏት። ከእነዚህም አንደኛው ባህላዊ ሙዚቃዎቿ ናቸው። ይህን ትልቅ ቅርስ ለማስፋፋት የትውን ጥበባት አካል የሆነው የሙዚቃ ትምህርት አንደኛው በመሆኑ በዚህ ክፍለ-ትምህርት በትኩረት ተመልክተናል።

ከዚህ አንጻር ክፍለ-ትምህርቱ በዋናነት ያካተተው በተማሪዎች በአካባቢ የሚገኙ የሃገረሰብ (ባህላዊ) ዜማዎች፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች እና የውዝዋዜ (የጭፈራ) አይነቶች በመሰብሰብና በመጫወት ላይ ሲሆን በዝርዝር የሚከተሉት መተግበር ከተማሪዎች ይጠበቃል።

- ከሥራ (ከእርሻና ከአርብቶ አደር ሥራዎች) ፣ ከሕብረት ፣ ከመልካም ሥነ ምግባርና ከበዓላት ሥነ ሥርዓቶች /ድርጊቶች/ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና ሙዚቃዎችን መሰብሰብ ፣ መተንተንና መጫወት

- ከባህላዊ ዘፈኖቹ ጋር በአካባቢያው የተለመዱ ቀላል የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን አቀናጅተው መጫወት

ትምህርቱን ለመተግበር በዋናነት የተለያዩ ተማሪ ተኮር ክንዋኔዎችና የማስተማር ዘዴዎችን ለማካተትም ተሞክሯል፡፡ የባለ ቀለም ወረቀት በመለጣጠፍ (የወረቀት ሞዛይክ) የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶችን በመቆራረጥ እንደየ ቀለማቸው በሥዕሉ ላይ በማጣበቂያ መለጠፍ ነው፡፡

በተጨማሪም የህትመት ስራ (ለምሳሌ የድንች ህትመት) ስንል ከላይ በክፍለ-ትምህርቱ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድን ድንች ሁለት ቦታ በመቁረጥ የምንፈልገውን ጽሁፍ ወይም ሥዕል በተቆረጠው በኩል ቀርጸንና ቀለምን ነክረን የምናትምበትን ሂደት ነው፡፡

በክፍለ-ትምህርቱ መጨረሻ ላይም ሃገረሰባዊ ታሪኮችን መንገር በሰፊው ቀርቧል፡፡ በዚህ ጽንሰ-ሀሳብ ዙሪያም በዋናነት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ሲተገበሩ የኖሩ የክንዋኔ ታሪኮችን ፣ ባህላዊ ስርአቶችን ፣ ስነ-ቃሎችን ወዘተ. በመስክ ጉብኝትና አንጋፋ የአካባቢው አባቶችን በመጋበዝ ልምድ እንድናገኝ እና ታሪካችንን እንድናውቅ አግዞናል፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. የምታውቋቸውን ቁምነገር አዘል ቆየት ያሉ ታሪኮች (ተረቶች) ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ
2. የዋሻ ጥበብን እና የቀለም ቅብን ታሪካዊ አመጣጥ አስረዱ፡፡
3. በአካባቢያችሁ ጥንታዊ የዋሻ ሥዕል አለ? ካለ ተወያዩበት፡፡
4. አንድ የባህል ዜማ ከውዝዋዜው ጋር በቡድን በማጥናት በክፍል ውስጥ አቅርቡ
5. የጋሞ የሴቶች ቀንን ታሪክ በጥልቀት ካነበባችሁ በኋላ በአካባቢያችሁ ያሉ ተመሳሳይ ታሪኮችን ከአባቶቻችሁ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡
6. የየራሳችሁን አዲስ ተረት በቡድን በመሆን ፍጠሩና በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማስተዋወቅ

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ-ትምህርት የትውን ጥበባት አንድነትንና ልዩነትን በስፋት ለማየት እንሞክራለን። ከዚህ በፊት በነበሩት ምዕራፎች ለማየት እንደሞከርነው ትውን ጥበባት ስንል ሙዚቃን፣ ውዝዋዜን ፣ የመድረክ ትወና ጥበብን የመሳሰሉትን አጠቃሎ የሚይዝ የትምህርት ዘርፍ ነው። በትውን ጥበብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የጥበብ ዘርፎች በመካከላቸው አንድ የሚያደርጓቸውና የሚለያይዋቸው ጽንሰ-ሃሳቦችን በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥ በተወሰነ መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

በዚህ ክፍለ-ትምህርት የተካተተው የእይታ ጥበባት በትምህርት የሚገኙ መሆናቸውንና ዕደ-ጥበብ ደግሞ በልምድ የምናገኘው የጥበብ አይነት መሆኑን ነው። የዕይታ ጥበባት ተብለው የሚጠቀሱት በርካቶች ናቸው ከእነዚህም መካከል ቅርፅ ፣ ቀለም ቅብ ፣ ጥቁረት/ንጣት ፣ መጠን እና የመሳሰሉትን በሰፊው እናገኛቸዋለን። ጥቁረት እና ንጣት እንዴት እንደሚገኝ ለሰላሳ እና ሸካራ እንዴት እንደምንለይ ፣ የአንድን ቁስ መጠን እንዴት እንደምንጠቀም ፣ ድግግሞሽ በምንስለው ሥዕል ላይ ሲደጋገም ምን ሊፈጥር እንደሚችል ስናስተውል ለህብረተሰባችን የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛና አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የዕደ-ጥበብ አይነቶች ወይም ውጤቶች በርካታ ሲሆኑ ለህብረተሰባችን እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ለአብነት የሸክላ ድስት ፣ ጀበና ፣ አልባሳት ባህላዊ አልባሳት፣ ገመድ፣ ቅርጫት ፣ የጥልፍ፣ ምንጣፍ ወይም መጋረጃ ለመስራት ወዘተ ያገለግላሉ። የዕደ ጥበብ ሥራዎች ለህብረተሰቡ ከሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች አንፃር አስፈላጊ በመሆናቸው ለተማሪዎች በሚከተለው መልኩ በዝርዝር በንድፈ ሀሳብ እና በተግባር ቀርበዋል።

## ከዚህ ክፍለ-ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁት አነስተኛ የመማር የብቃት አሃዶች፡-

- በትውን ጥበባት ውስጥ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን በተግባር ያቀርባሉ፡፡
- የእይታ ጥበብና እደ-ጥበብ በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡

# 4.1. በትውን ጥበብ ውስጥ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን መወያየት

### መግቢያ

የሰዉ ልጅ የትውን ጥበባትን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀምባቸዋል፡፡ ከአገልግሎቶቹ ጥቂቶቹ ለህክምና በተለይም የአእምሮ ጭንቀትን ለማስወገድ  በሙዚቃ አማካኝነት ከህመሙ እንዲፈወስ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ ለመደሰቻ፣ ለአምልኮት፣ ለሀዘን መግለጫ፣ ለማስተማሪ፣ ለተለያዩ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች ፣ ለግንዛቤ መፍጠሪያ፣ ለገቢ ማስገኛ ልጠቀምባቸው ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ትውን ጥበባት ለአንድ ኅብረተሰብ አስፈላጊ እንደሆኑና ከብዙዎቹ የሰው ልጅ ክንዋኔዎች ጋር በቅርብ የተቆራኙ ናቸው፡፡ ማንኛውም የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ሰብእና እድገትን ለሚሟላት ከሚያስፈልጉት አንደኛው የትምህርት ዘርፍ ትውን ጥበብ እንደሆነ በተለያዩ ባለሙያዎች ተሰምሮበታል፡፡  በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥም ተማሪዎች በትውን ጥበባት ውስጥ ያሉ የሃሳብ አንድነትና ልዩነቶችን እንዲረዱ እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ያላቸውን አንድነትና ልዩነት መረዳት እንዲችሉ ማገዝ አስፈላጊ ነው፡፡

## ከዚህ ትምህርት መጨረሻ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- በትውን ጥበባት ውስጥ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን ይረዳሉ፡፡
- በትውን ጥበባት ውስጥ ያሉ የሃሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን በክዋኔ ያቀርባሉ፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

- የቴአትርን ፣ የሙዚቃን እና የውዝዋዜን አንድነትና ልዩነት ተወያዩ

## 4.1.1. 4.1.1. የትውን ጥበባት አንድነትና ልዩነት

**አንድነቶች፡-**

- ሁሉም ተሰጥኦን ማዕከል ያደረጉ ናቸው

- ሁሉም ስሜትን ፣ አስተሳሰብን ፣ ማንነትንና የመሳሰሉትን ይገልጻሉ
- ማህበረሰብን የማስተማር (የመለወጥ) አቅም አላቸው
- ማህበረሰብን የማዝናናት ሚናን ይጫወታሉ
- ሀገርን በገቢ ይደግፋሉ
- ባህልን ያስቀጥላሉ
- ብዙ የማህበረሰብ አካባቢ ጋር በቀላሉ ይደርሳሉ
- ለተጨቆኑ በተለያየ መንገድ መልእክትን በማስተላለፍ ድምጽ ይሆናሉ

**ልዩነቶች፡-**

- መገለጫ መንገዳቸው የተለያየ መሆኑ (ለምሳሌ፡- ሙዚቃ መስማትን ማእከል ሲያደርግ ፣ ውዝዋዜ ደግሞ አካላዊ እንቅስቃሴን ማእከል ያደርጋል እንዲሁም ቴአትር የመድረክ ትወናን ማእከል ያደርጋል)
- አንዳንዶቹ ጥበባት በህዝብ ፊት የሚቀርቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በመስሪያ ቦታ ተሰርተው (ተመርተው) ካለቁ በኋላ ለእይታ የሚቀርቡ ናቸው።

የትውን ጥበብ የምንላቸው ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ሙዚቃ
- ቴአትር
- ውዝዋዜ

የመሳሰሉት ናቸው። የትውን ጥበባትን ስራ የሚያቀርቡ ሰዎች የትውን ጥበባት ባለሞያዎች ይባላሉ። ሁሉንም የትውን ጥበባት አይነቶችን ለመተግበር አእምሮም አካልም በቅንጅት መስራት ይኖርበታል።

ለምሳሌ ተከታዩን መዝሙር እንመልከት

### ፀሀዬ

ፀሀዬ....ደመቀች
ደመቀች
ብርሀኗን ለኛ ማለት
አ...ዎ
አወቀች /2 ጊዜ/
ፀሀይ ብርሀን ፈንጠቃ
ካድማስ ወደኛ መጥቃ
ጊ....ዜ /2 ጊዜ/
ደመቀ ጠራ ሰማይ
በእናት ሀገር በእማይ

ደመቀ ጠራ ሰማይ
በእናት ሀገር በእማይ

ከላይ የተቀመጠውን መዝሙር ለመዘመር አእምሮና አካል በጥምረት መስራት ይኖርባችኋል፡፡

**መልመጃ 4.1**

1. የትውን ጥበባት አንድነት የምንላቸውን ዘርዝሩ
2. የትውን ጥበባት ልዩነት የምንላቸውን ዘርዝሩ

## 4.2. የእይታ ጥበብ እና ዕደ-ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው አስፈላጊነት

### መግቢያ

የእይታ ጥበብ እና ዕደ-ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው አስፈላጊነት ስንል ከእነዚህ የጥበብ ስራዎች ለህብረተሰባችን ከሚሰጡት የጥበብ ስራ አንጻር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ይህም የጥበብ ስራ አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታመን ሲሆን የቀለም ቅብ ስራ ካላቸው ጠቀሜታ አንጻርም ከዚሁም የጥበብ ስራ የሚመደብ ነው በተመሳሳይም የዕደ ጥበብ ስራዎችም ለቤት ቁሳቁስ መገልገያነት ለጌጣጌጥ ስራዎች ለአልባሳትነት በእጅ ሞያ የሚሰሩ እና አስፈላጊ ሆነው ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው፡፡

### ከዚህ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች የቀለም ቅብ ስራን በሚገባ ይገነዘባሉ
- ተማሪዎች የዕደ ጥበብ ውጤቶችን ስለው ያሳያሉ
- ተማሪዎች የዕደ ጥበበ ውጤቶችን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ተማሪዎች የዕይታ ጥበብ ስራዎች በህብረተሰባችን ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
- ተማሪዎች የዕደ ጥበብ ስራዎች በህብረተሰባችን ውስጥ ያላቸውን አስፈላጊነት አብራሩ፡፡

### 4.2.1. የዕይታ ጥበብ

የእይታ ጥበባት የምንላቸው የጥበብ ባለሞያዎች ሃሳባቸውን እና የተለያዩ መረጃዎችን በሚስብ መልኩ ለእይታ ማዘጋጀት ነው። የእይታ ጥበብ ከምንላቸው መካከል፦

- ንድፍ
- ህትመት
- ኪነ ቅርጽ
- የቀለም ቅብ
- ፎቶ ግራፍ

### 4.2.2. 4.2.2 የዕደ ጥበብ

- የሽመና ስራ
- የቅርጫት ስራ
- የጥልፍ ስራ
- የሸክላ ስራ
- የገመድ ስራ

ዕደ-ጥበብ ማለት ማንኛውም ሰው በልምድ የሚሰራው የጥበብ አይነት ነው። የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን የምናገኝባቸው ዘዴዎች ብዙ አይነት ሲሆኑ ለመጥቀስ ያህልም በህብረተሰቡ ውስጥ እናገኛቸዋለን።

**ለምሳሌ፡-**

#### ሀ. የሸክላ ስራ

የሸክላ ስራ ውጤቶች ከአካባቢያችን ከምናገኛቸው የአፈር አይነቶች የምንሰራቸው የዕደ-ጥበብ ውጤቶች ሲሆኑ የምንጠቀማቸው የአፈር አይነቶችም ለሸክላ ስራ የተመረጡ እና የሚመቹ መሆን አለባቸው። አዘገጃጀቱም በጥንቃቄና ትክክለኛውን መንገድ በመከተል መሆን አለበት።

የሸክላ ስራን ለመስራት ቀይ አፈር፣ ጥቁር አፈር ወይም ሌላ የአፈር አይነት መጠቀም የምንችል ሲሆን አፈሮቹን ደባልቀን መስራት ግን አንችልም። ምክንያቱም የመሰንጠቅ ባህሪ ሊያመጣ ከመቻሉም በላይ የምፈልገውን ቅርጽ በቀላሉ ማግኘት አዳጋች ይሆንብናል። የሸክላ ጥበብ ስራዎችን ለቤት መገልገያ እንደ ጀበና፣ ሸክላ ድስት፣ ምጣድ እና ማሰሮ እንዲሁም ለተለያዩ ጌጣ ጌጦችን ለመስራት እንጠቀምባቸዋለን።

**መልመጃ 4.2**

1. የሸክላ አሰራር ቅደም ተከተሎችን ግለጹ
2. ሞዴል የሸክላ ስራ ሰርታችሁ አቅርቡ

#### ለ. ሽመና

የሽመና ስራ በአካባቢያችን ሆነ በሀገራችን በዋነኝነት ከሚታወቁ የዕደ-ጥበብ ውጤት አንዱ ነው። የሽመና ስራ መገልገያ መሳሪያዎች እንደ ጥጥ እና ከተለያዩ ቀለማት የሚሰራ ክር የሚዘጋጁ ናቸው። ሽመና ስራ በዚህ ሞያ የሰለጠኑ ወይም በልምድ

የሚሰሩ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰራ የአልባሳት የጥበብ አይነት ነው።

**መልመጃ 4.3**

1. ሽመና ለመስራት ምን ያስፈ.ጋል?
2. የሽመና ውጤቶች በዝርዝር አብራሩ።

## ሐ. የገመድ ስራ

የገመድ ስራ በአካባቢያችን ብሎም በሀገራችን ከሚገኙ የዕደ ጥበብ ዘርፍ ውስጥ አንዱ ነው። ገመድ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንዱን እንደ ምሳሌ ብንወስድ ለስፓርታዊ ወድድር እና ለተለያዩ የቤት ውስጥ ግልጋሎት ይውላል። ገመድ ከቃጫ ፣ ሲባጎ ፣ ከማዳበሪያ ወይም ከክር ይሰራል። የገመድ ስራ በሦስት በተነጣጠሉ ቃጫ ወይም በባለ ሁለት በተከፋፈለ ቃጫ የሚሰራ ሲሆን ይህንን ቃጫ የምናገኘው ከእንሰት ተክል ነው።



ምስል 4.1: የገመድ ስራ ውጤት

**መልመጃ 4.4**

1. የባለ ሁለት ገመድ አሰራርን ግለጹ።
2. ገመድ ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው?

## መ. የቅርጫት ስራ

ቅርጫት ለህብረተሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ነው። ቅርጫት በአካባቢያችን ከምናገኘው የቀርከሀ እንጨት የሚሰራ ነው። ይህ የቅርጫት ስራ በማህበረሰብ ውስጥ በልምድ የሚገኝ የዕደ-ጥበብ ሙያ ሲሆን ለህብረተሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ሰፊ እንደሆነ ይታወቃል። ለአብነት ዶሮ ለማርባት ፣ ጥራጥሬዎችንና ፍራፍሬን ለመያዝ እና ሌሎች ቁሳቁሶችንም ማስቀመጫ ሆኖ ያገለግላል። የቅርጫት ስራ ስንል ዘንቢል ስራን፣ ከሳር የሚሰራ ስጋጃ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችንም ያጠቃልላል።



ምስል 4.2: የቅርጫት ስራ ውጤት

**መልመጃ 4.5**

1. የቅርጫት ስራን በቡድን ሆናችሁ ሰርታችሁ አሳዩ።
2. የቅርጫት ስራ ለምን እንደሚያስፈልግ በዝርዝር አብራሩ።

### ሠ. የጥልፍ ስራ

የጥልፍ ስራ በአካባቢያችንም ሆነ በሀገራችን በስፋት የሚታወቅ በትምህርት እና በልምድ የምናገኘው የዕደ-ጥበብ አይነት ነው። በማህበረሰባችን ውስጥ ከምናያቸው አልባሳት ፣ ምንጣፍ ፣ የቁሳቁስ መሸፈኛ አልባሳት እና ለተለያዩ ጥቅሶች መፃፊያ የሚጠቅም የዕደ ጥበብ አይነት ነው። የጥልፍ ስራ በህብረተሰቡ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ እና ተፈላጊም ጭምር ነው ። ይህ የዕደ ጥበብ ስራ መርፌና የተለያዩ የመጥለፊያ ቁሳቁስን በመጠቀም እና ቀለም ያላቸው የክር አይነቶችን በመጠቀም ዲዛይኖችን በሥዕልና በፅሁፍ መልክ በመንደፍ የሚሰራ ነው።



ምስል 4.3: የጥልፍ ስራ ስዕላዊ መግለጫ



ምስል 4.4: የአልባሳት ዲዛይኖች

**መልመጃ 4.6**

1. ለጥልፍ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው?
2. ተማሪዎች ስማችሁን በጥልፍ ስራ ሰርታችሁ በክፍል ውስጥ አሳዩ ፡፡

## ማጠቃለያ

የትውን ጥበባት ሃሳቦቻችንን፣ ስሜቶቻችንን፣ አስተያየቶቻችንን እንዲሁም ምርጫዎቻችንን በትውን ጥበባት ማለትም በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በቴአትር ጥበብ፣ በሰርከስ በመሳሰሉት የምንገልጽበት የጥበብ ዘርፍ መሆኑን አይተናል፡፡

የትውን ጥበባት በመሰረቱ በተመልካች ፊት ሊቀርቡ የሚችሉ የጥበባት አይነቶች ናቸው፡፡ ስራውን የሚያቀርቡ ሰዎች ደግሞ የትውን ጥበብ ባለሞያዎች ይባላሉ፡፡ ሁሉም የትውን ጥበባት አይነቶች ከጀርባቸው ትልቅ የሆነ የፈጠራ ሀይል አላቸው፡፡ እነዚህን ጥበባት ለመተግበርም የአዕምሮና የአካል ጥምረት ይፈልጋል፡፡ በዚህ ክፍለ-ትምህርት ውስጥ ያየነው የእይታ ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ሲሆን ከዚህም ጋር በተያያዘ በቀለም ቅብ ስራ ጥበብ ውስጥ ቀለሞችን በማዋሃድ በግርግዳዎች፣ በጨርቆችና ላሜራ ብረቶች ላይ ሥዕሎችን መስራት እንደምንችል አይተናል፡፡ የአካባቢያችንን ታሪካዊ ቦታዎች ማስተዋወቅም አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ በቅርጽ (ስነ-ህውልት) ስራ ላይም የአካባቢያችንን ታዋቂ ሰዎችና ታሪካዊ ቦታዎችን በመቅረጽ ማህበረሰቡ ስለ እራሱ ባህልና እሴት ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ እንደምንችል አይተናል፡፡ የዕደ-ጥበብ ስራ በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታም በዚሁ የትምህርት ክፍል ውስጥ የተካተተ ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡

## የማጠቃለያ መልመጃ

1. ፀሀዬ የሚለውን መዝሙር ጥንድ ጥንድ በመሆን ዘምሩ፡፡
2. አካባቢያችሁ ስለሚገኙ ታሪካዊ ስፍራዎች ውይይት አድርጉ፡፡
3. የሸክላ ስራ ለመስራት የምንከተላቸውን ቅደም ተከተሎች ዘርዝሩ
4. ተማሪዎች የምትወዱትን ዲዛይን በጥልፍ ስራ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
5. ተማሪዎች ገመድን ከምን ከምን መስራት እንችላለን?

# ምዕራፍ አምስት

## 5. መስተጋብር

### መግቢያ

መዝሙር ድምጽን በማውጣት፣ ቃላትን በመጠቀም፣ ሙዚቃዊ ዜማ ባላቸው፣ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ የተለያዩ መልዕክቶች ለማስተላለፍ የሚረዳን አንዱ የሙዚቃ ክፍል ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን የትውን ጥበብ ዘርፍ የሆነ የማስተማርያ ስነ-ዘዴን በመጠቀም አንገብጋቢ የሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮችን ልጆች በቀላሉ ተረድተው እንዲዘምሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማስፋት ይቻላል፡፡ ይህን ማለት እንደ የትራፊክ ደህንነት ጽንሰ-ሀሳብ ፣ የ ኤች አይ ቪ ኤድስ ፣ የአደንዛዥ ዕጽ አስከፊነት የመሳሰሉትን ጉዳዮች መዝሙርን እንደ መሳርያ በመጠቀም በክፍለ-ትምህርቱ የተቀመጠውን የብቃት አሀድ ማሳካት ይቻላል፡፡

መዝሙር የውስጥ ስሜትን በመኮርኮር ሊያስተምር፣ ሊያስደስት፣ ሊያስጨፍር፣ ሊያስተክዝና ብሎም ሊያሳዝን ይችላል፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በመዝሙር አማካይነት ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ጓደኛ፣ አብሮ ስለመኖርና ስለ ሀገር ፍቅር፣ ከበሽታ እራስን ስለመጠበቅ፣ ስለትራፊክ መንገድ አጠቃቀም፣ ስለ ሱስ አስከፊነት በአጠቃላይ ማሕበራዊ ኑሮአቸውን ለማሸነፍና የእውቀት አድማሳቸውን ለማስፋት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

በተጨማሪ በዚህ ክፍለ-ትምህርት የምናየው ስለምልክቶችና አርማዎች ነው፡፡ ምልክቶች ለበርካታ አመታት ለህብረተሰባችን አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን በስፋት አንድን መልእክት በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማግኘት ይረዳናል፡፡ አርማዎች በአንጻሩ የተለያዩ ተቋማት መለያዎችን የያዙ የመግባቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡

## በዚህ ክፍለ-ትምህርት ከተማሪዎች የሚጠበቁት የመማር የብቃት የሚከተሉት ናቸው

- መዝሙሮችን ፣ ውዝዋዜዎችን እንዲሁም የመድረክ ትወናዎችን አንገብጋቢ ርዕሰ-ጉዳይ ከሆኑት (የትራፊክ ደህንነት ፣ ኤች አይ ቪ ፣ የአደንዛዥ እጽ አስከፊነት) ከመሳሰሉት ጋር በማቀናጀት ያቀርባሉ
- በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የመግባቢያ ምልክቶችን (አርማ ፣ ፖስተር....) የመሳሰሉትን ይረዳሉ
- ተማሪዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ አርማና ምልክቶችን በቡድን ተወያይተው ገለፃ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ምልክቶችን እና አርማዎችን በክፍል ውስጥ ያዘጋጃሉ

## 5.1. ሰርቶ ማሳየት

### መግቢያ

በዚህ ርእስ ስር ልጆች ወቅታዊና አንገብጋቢ የሆኑ ጉዳዮችን በመዝሙር በጥንድና በህብረት በመሆን እየዘመሩና እየተዝናኑ ቁም ነገር ይጨብጣሉ፡፡ ስለሆነም ይሄ ርእስ ከትራፊክ ደህንነት፣ ከኤች አይቪ ኤድስ እንዲሁም ከአደንዛዥ እጽ ጎጂነት ከመሳሰሉት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ  መዝሙሮችን ሰርቶ ማሳየት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

### ከዚህ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- መዝሙሮችን ወቅታዊ ርዕሰ-ጉዳይ ከሆኑት (የትራፊክ ደህንነት፣ ኤች አይ ቪ፣ የአደንዛዥ እጽ አስከፊነት) ከመሳሰሉት ጋር በማቀናጀት ያቀርባሉ፡፡

### የመወያያ ጥያቄ

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት የምታውቁትን ስለ ትራፊክ ደህንነት፣ ስለ ወረርሽኝ እና በሽታ መዝሙር ዘምሩ፡፡

### መዝሙር 1 ፡- ኤች አይ ቪን እናጥፋ

የሰው ሰውነቱ የእድገት መሰረቱ
ሥራ ነው ሥራ ነው አለኝታ ሕይወቱ } **አዝማች 2 ጊዜ**

ተከብሮ የመኖር የእድገት ዋስትናችን
ሥራ ነው ሥራ ነው ፍፁም ሕይወታችን
ከ ኤች አይ ቪ እንጠብቅ እራሳችንን
ለማልማት እንድንችል ሀገራችንን
እኛ ተማሪዎች ኤች አይ ቪን አጥፍተን
ሀገር እንድታድግ እንስራ በርትተን

**አዝማች 2 ጊዜ**


## መዝሙር 2፡- የትራፊክ መብራቶች



ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ተሽከርካሪ ሲቆም እኔ እሻገራለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ተሽከርካሪ ሲቆም እኔ እሻገራለሁ
በራ አረንጓዴ በራ
በራ አረንጓዴ በራ



የተሽከርካሪ ነው ሳይሆን የኔ ተራ
የተሽከርካሪ ነው ሳይሆን የኔ ተራ
በራ ቀዩ መብራት በራ
በራ ቀዩ መብራት በራ
መኪናው ቆመልኝ እኔ ልሻገራ
መኪናው ቆመልኝ እኔ ልሻገራ



ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ተሽከርካሪ ሲቆም እኔ እሻገራለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ግራ ቀኝ ግራ ሁሉንም አያለሁ
ተሽከርካሪ ሲቆም እኔ እሻገራለሁ

**መዝሙር 3፡- አደንዛዥ እጽን እንጸየፍ**





ከደንዛዥ እጽ እንራቅ
ጤናችንን እንጠብቅ
ከአልኮል መጠጥ እንራቅ
ጤናችንን እንጠብቅ
ከሲጋራ ሱስ እንራቅ
አዕምሯችንን እንጠብቅ
ከሱሶች ሁሉ እንራቅ
ክብራችንን እንጠብቅ
ጫት መቃምን እንጠየፍ
ለሃገር ልማት እንሰለፍ

**መልመጃ 5.1**

1. 1. የሚከተለውን ግጥም የራሳችሁን ዜማ ፈጥራችሁ በቡድን ዘምሩ

**መዝሙር 4**

**ኤድስ እንዳያጠቃን**

አስከፊው በሽታ ኤድስ እንዳያጠቃን
እኛ ተማሪዎች መጠንቀቅ አለብን
በዓለም ዙሪያ ሁሉ ህዝብን የበከለው
በሕክምና ዘርፍ መፍትሄ የሌለው
የሰው ልጆች ጠላት ቀሳፊዉ ኤድስ ነው
እንከላከለው ዛሬ ነገ ሳንል
የሀኪሞችን ምክር ሁሉም በመቀበል
ጥቁር ነጭ የማይመርጥ ድንበር ማያግደው
ሕጻን ሽማግሌ ጾታ የማይለየው
ሁሉንም ይፈጃል ቀሳፊዉ በሽታ
ካልተጠነቀቅን አይሰጠንም ፋታ




2. የሚከተለውን ግጥም የራሳችሁን ዜማ ፈጥራችሁ በቡድን ዘምሩ

**መዝሙር 5**

## ጠንቃቃ ተማሪ

ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ
ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ
የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል
የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል፡፡ } አዝማች

የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን
መኪና ይቆማል ጠብቆ ህጉን
ወንዝ ስንሻገር ግራ ቀኝ አይተን
መጠንቀቅ አለብን ድልድይ ላይ ሆነን
ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ
ሀሳቡን ሰብሰቦ በመንገድ ተሻጋሪ
የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል
የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል



3. የሚከተለውን ግጥም የራሳችሁን ዜማ ፈጥራችሁ በቡድን ዘምሩ

**መዝሙር 6፡- ደኑ ለሕይወቴ**

አዝ 2 ጊዜ { አልሁኝ እኔው ለኔ ደኑ ለሕይወቴ
ብሎም ለወገኔ ለርሃብ መድሃኒቴ

ለሕንፃው ለጎጆው ዋልታና ማገሩ
ለርሻ መሣሪያዎች ለሞፈር ቀንበሩ
ለሸማኔው እቃ ለቅሉ ለእንዝርቱ
ደን ነው መሰረት ደን ነው ሕይወቱ

አዝ 2 ጊዜ

ባህር ዛፍ ቀረሮ ዝግባ ሆነ ጽዱ
ለአፈር ጥበቃ ይብዛ በመንገዱ
ይሁን ባህላችን ችግኝን ማፍላት
አፈር መንከባከብ ውሃ ማጠጣት

4. የሚከተለውን ግጥም የራሳችሁን ዜማ ፈጥራችሁ በቡድን ዘምሩ

**መዝሙር 7**

**ውሀ**

አዝ 2 ጊዜ { ጊዜ ሽታህ አይታወቅ መአዛ የለህ
የፍጥረት አለኝታ አንተ ውሀ ነህ



የተፈጥሮ ፀጋ ቋሚ ለህይወት
ማን አለ እንደ ውሀ ለሰው ልጅ ልማት
ውሀ ተበክሎ በሽታ እንዳይወልድ
ወንዞችን ማፅዳት ነው በግድም በውድ

አዝ 2 ጊዜ

ለደናችን ውበት ዋልታና ማገሩ
ለኃይላችን ምንጭ ውሃ ላይ ምከሩ
ብዙ ብንመራመር ብናስብ በአንክሮ
ውሃን የሚተካ የለም ከተፈጥሮ

**መዝሙር 8፡-** **እጽዋት**

እንትከል እጽዋትን ከዘር ጀምሮ
እንመግባቸው ፀሐይ ውሀ አፈር ጨምሮ
ፈክተው ወደ አበባነት እንዲቀየሩ
እየኮተኮትናቸው እናድርግ እንዲያምሩ

## 5.2. በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ምልክቶች እና ዓርማዎች

### መግቢያ

በህብረተሰባችን ውስጥ በርካታ የሆኑ ህብረተሰባችን የሚጠቀሙዋቸው እና የሚገለገሉባቸው ምልክቶች እና አርማዎች አሉ፡፡ እነዚህም አርማዎች ከትውልድ ትውልድ እየመጡ እና የራሳቸው መለያና መገኛ ቦታዎችን የሚጠቁሙ መንገዶች ናቸው፡፡ ምልክቶች በበርካታ ስፍራዎች ህብረተሰቡ የሚፈልጉዋቸውን አቅጣጫ ወይም ቦታ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አርማዎችም የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም የራሱ መለያ እንዳለው የሚያመለክት ሲሆን ያንኑ ድርጅት ወያም ተቋም የሚወክል ነው፡፡ በጥቅሉ እነዚህ ምልክቶች እና አርማዎች የተለመዱ ለህብረተሰባችን አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

### ከዚህ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ምልክቶች እነማን እንደሆኑ ይረዳሉ
- ተማሪዎች በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ምልክቶችን በደብተራቹ ወይም በጨርቅ ላያ ሥለው ያሳያሉ
- ተማሪዎች  በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ አርማዎች ምን እንደሆኑ ይገልጻሉ

### የመወያያ ጥያቄዎች

- ❖ ተማሪዎች በአራተኛ ክፍል ውስጥ የተማራችሁትን የምልክት አይነቶችን በቡድን ተወያይታቹ ለክፍል ተማሪዎች ግለጹ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከዚህ በፊት የተማራችኋቸውን የአርማ አይነቶችን በቡድን ተወያይታቹ ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ


### ሀ. ቀላል ምልክቶች

ምልክቶች የምንላቸው በአንድ ህብረተሰብ ወይም አካባቢ ውስጥ ስለ አንድ ተቋም ወይም ድርጅት እንዲሁም የህዝብ አገልግሎት እና ስፍራ በቀላሉ በሥዕል ወይም በፅሁፍ መልክ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ቦታ ጠቋሚና መልእክት ማስተላለፊያ ሥዕላዊ መግለጫ ነው፡፡

ምልክት ብለን የምንጠራቸው ለምሳሌ የእግረኛ መተላለፊያ የሚያሳይ ምልክት (ዜብራ) ፣ ሆቴሎች እና የህዝብ መዝናኛ አካባቢ የምናገኛቸው መረጃ ሰጪ ሥዕሎችን ነው፡፡




ምስል 5.1: የእግረኛ ማቋረጫ (ዜብራ)



ምስል 5.2: መስቀለኛ መንገድ ጠቋሚ



ምስል 5.3: የትራፊክ መብራት ምልክት



ምስል 5.4: የእንሣት መተላለፊያ መንገድ



ምስል 5.5: የሴቶች መጸዳጃ ቤት ምልክት ፣ የወንዶች መጸዳጃ ቤት ምልክት

## መልመጃ 5.2

1. በአካባቢያችሁ ያሉ ምልክቶችን በሥዕል ሰርታችሁ አሳዩ
2. በአካባቢያችሁ ያሉ ምልክቶችን ይጠቀማሉ ወይም አይጠቀሙም በሚል በሁለት ቡድን ሆናችሁ ተወያዩ
3. በአካባቢያችሁ የማይገኙ ምልክቶች ግን በአካባቢው ቢኖሩ ጥሩ ነው የምትሏቸውን ምልክቶች ስላችሁ አሳዩ

4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ምልክቶችን በእንጨት ላይ ሰርታችሁ አሳዩ
5. የምትማሩበትን ትምህርት ቤት የሚገልፅ ምልክት በራሳችሁ አገላለፅ ሰርታችሁ አቅርቡ

## ለ. ዓርማ

ዓርማ በጽሁፍ ወይም በሥዕል የሚገለጽ ሲሆን የግል ወይም የመንግስት ድርጅት እንዲሁም ተቋማትን መግለጫ ምልክት ነው። ዓርማዎች በጨርቅ ወይም በወረቀት ላይ የታተሙ ሆነው የተቋሙን መግለጫ መልእክት የሚያስተላልፉና የሚያስተዋውቁ መለያ ምልክቶች ናቸው። ዓርማን ስንጠቀም የታወቁ ወይም ጥቃቅንና አነስተኛ የስራ ዘርፎች ውስጥ ያሉ ድርጅቶችን እንዲሁም መስሪያ ቤቶችን ስሞች በአጭሩ በመፃፍ ወይም በመሳል ነው። እንደ ኮካ ኮላ አርማ በአለም ላይ የሚታወቅ ምልክትን በቀላሉ ለማስታወስ እና ለማየት ይረዳናል።

### የአርማዎች ምሳሌ ፡-



ምስል 5.6: የኢትዮጲያ ባንዲራ ላይ ያለው የኮከብ ምስል

ምስል 5.7: የኮካ ኮላ አርማ



ምስል 5.8: በደቡብ ባንዲራ ላይ ያለው የጎጆ ቤት ምስል

ምስል 5.9: የቀይ መስቀል ምልክት

### መልመጃ 5.3

1. በአካቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ የድርጅት ዓርማዎችን ስላችሁ አሳዩ።
2. ዓርማ ለምን እንደሚጠቅም በፅሁፍ ግለጹ።
3. ዓርማዎች ከምን ከምን እንደሚሰሩ ግለጹ።
4. ዓርማ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሰሌዳ ላይ ስላችሁ አሳዩ
5. ተማሪዎች በራሳቸው ስም ድርጅት ሰይማችሁ አርማ ስሩ

# ማጠቃለያ

መዝሙር ድምጽን በማውጣት ፣ ቃላትን በመጠቀም ፣ ሙዚቃዊ ዜማ ባላቸው ፣ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ የተለያዩ መልዕክቶች ለማስተላለፍ የሚረዳን አንዱ የሙዚቃ ክፍል መሆኑን በዚህ ክፍለ ትምህርት ለማየት ሞክረናል፡፡ ይህንን የትውን ጥበብ ዘርፍ በመጠቀም አንገብጋቢ የሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮችን ልጆች በቀላሉ ተረድተው እንዲዘምሩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን ማስፋት ተችሏል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የትራፊክ ደህንነት ጽንሰ-ሀሳብ፣ የ ኤች አይ ቪ ኤድስ ፣ የአደንዛዥ ዕጽ አስከፊነት የመሳሰሉትን ጉዳዮች መዝሙርን እንደ መሳርያ በመጠቀም ለማስተማር እንደተቻለ እናምናለን፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ክፍለ ትምህርት ምልክት ማለት ህብረተሰቡ የሚጠቀማችው መረጃ ሰጪ ፣ መረጃ ጠቋሚ እና አድራሻ ጠቋሚ መሆናቸውን አይተናል፡፡ አርማ ማለት ደግሞ በህብረተሰብ ውስጥ የምንገለገልባቸው የተለያዩ የግል እና የመንግስት ተቋማትን መለያ የያዙ ወይም ተቋማትና ድርጅቶችን የሚገልጹ (የሚወክሉ) መገለጫዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተካተቱትን ሃሳቦች በሰፊው በመተግበር ግንዛቤያችሁን አሳድጉ፡፡

# የመልመጃ ጥያቄዎች

1. በአካቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ ምልክቶችንና የድርጅት ዓርማዎችን ለይታችሁ በማውጣት ተወያዩባቸው፡፡
2. የኮሮና በሽታ ላይ የሚያተኩር አጠር ያለ ግጥም ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመጻፍ ዜማ ፈጠራችሁለት ዘምሩ፡፡

# ዋቢ መጽሐፍት


- የ ከ5ኛ-6ኛ ክፍሎች ሙዚቃ የተማሪ መፅሐፍ በአ/አ/ከ/አስ/ት/ቢሮ 1997
- የሙዚቃ ትምህርት ለወጣት ተማሪዎች ሁለተናዊ እድገት ያለው ጠቀሜታ አ.አ 2004 ደበሬ አብዲሳ ያልታተመ
- በክልል 14 የትምህርት ቢሮ (1988 ዓ.ም) ሙዚቃ የመምህሩ መምሪያ አምስተኛ ክፍል ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራዝ